# ፍጹም-የማያቋርጥ
# ከአለቱ የወጣ ውኃ

ዛሬ ጠዋት ስለ ጌታ እግዚአብሔር መገኘት እናመሰግናለን፡ መልእክትን በመስጠት የማለዳውን ጉባኤ ይጀምራልና፡ እ—እኛም በፊቱ ይህን “መስማት፡ ዝቅ ማለት” አለብን፡ አንዳች ነገር ይናገረናልና። የገባውን ቃል እንደሚፈጽም እርግጠኛ ነኝ። ሁል ጊዜ ቃሉን ይጠብቃል። እናም ዛሬ ጠዋት በአንድነት፡ በህያውነት፡ እና ዛሬ ጥዋት በዘላለም በአንዱ ጥግ ስለተሰበሰብን፡ እንደገናም ማምለክ ስለ ቻልን፡ እንዲሁም ተሰብሰበን ከእርሱ መስማት ስለሆነልን እናመሰግናለን። አንድ ላይ የምንሰበሰብበት ምክንያቱ፡ ለዚህ ዓላማ ነው።

2 አሁን፡ ባልተጠበቀ መንገድ፡ ባየሁት ህልም ምክንያት፡ ዛሬ፡ በድንገት በድንገት ተገኝቼ ለወንድም ኔቪል ዱብ ዕዳ ሆኜበታለሁ። እኔ... በሕልም... እ... አምናለሁ። እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር በሕልም ይገናኛቸዋል። እና ባለፈው ምሽት፡ በጣም ያልተለመደ ህልም አየሁ። በዚህ ህልም ውስጥ፡ በአንድ ኮረብታ አካባቢ ላይ፡ በኮረብታው ላይ እየተራመድኩ ነበር፡ እና እ—እራቴን ልበላ ወደ ምግብ ቤት እየሄድኩ ነበር። እናም ወደ ቦታው ሰጠጋ፡ ይህን አስተዋልሁ፡ ሙዚቃ እየተጫወቱ ነበር፡ ኦርኬስትራ ሙዚቃ ሲጫወቱ፡ ከቫዮሊን ጋር፡ ምግባቸውን እየተመገቡ ህዝቡን ሲያዝናኑት አየሁ። እናም በዚያ ላይ ያልወደድኩለት ነገር ስለ ነበር፡ ነገሩን ችላ ብዬ አለፍኩ። እና ወደ ኮረብታው የሚወጣ ሰው አገኘሁ። አየሁም፡ እነሆም ብዙ ሰዎች ወደዚህ ምግብ ቤት ለመሄድ ወደ ኮረብታው እየወጡ ነበር። እኔ ግን ከእነሱ ርቄ፡ ወደ ቀኝ፡ ወይም፡ ወደ ግራ ዞርኩ።

3 እና በሆነ መንገድ፡ በሸለቆው ውስጥ፡ ተበርናክሉ ይታየኝ ነበር። እንዲህም ሲናገር፡ የአንድ ሰው ድምፅ ሰማሁ፡ “እንዲህ-እንዲያ በተባለው መሻገሪያ ላይ ከወንድም ብራንሃም ጋር ተገናኝ። በዚያ በኩል ከተራራው እየወረደ ነውና። እንዲህ-እና-እንዲህ ያለ ነገር ንገረው።” እኔም ወደ መሻገሪያው ለመድረስ እየተቻኮልኩ ነበር።

4 ሰውዬው በደረሰ ጊዜ፡ እነሆ ቡኒ ልብሰ የለበሰው ወንድም ኔቪል ነበር፡ ልክ ዛሬ ጥዋት ተቀምጦ እንዳለው ምስሉ ይመስላል። እርሱም፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ከተማ ውስጥ የምትቆይ ከሆነ፡” አለኝም፡ “ብትወርድ የ—የተሻለ ይሆናል፡ ምክንያቱም ወንድም ሃንክ... ” እንግዲህ፡ ወንድም ሃንክ በመባል የማውቀው፡ ብቸኛው ወንድም፡ ወንድማችን ሄንሪ ካርልሰንን ነው፡ ሃንክ ብለን እንጠራዋለንና። አለኝም፡ “ከተማ ውስጥ የምትገኝ ከሆነ ተበርናክሉን አለመጎብኘትህ እንግዳ ነገር ነው ብሎ ያስብ ይሆናል፡ ምናልባት በከተማ ዙሪያ ለጥቂት ቀናት ከቆየህ።” አለኝና ነቃሁ።

5 እና፡ በዛ ላይ፡ እንግዳ ነገር ተሰማኝ። በዚያ በሳምንቱ ውስጥ ምናልባት ወንድም ኔቪል ለዛሬ ማለዳ፡ ለቤተክርስቲያን ያዘጋጀው ስፔሻል ነገር መኖሩን

እስክጠይቀው ድረስ፡ ጣልቃ ልገባበት አልፈለግኩም ነበር። ስለዚህም እንደ ሁልጊዜው፡ ደግ ሆነልኝና፡ “ና ውረድ፡” አለኝ። ስለዚህም፡ መጣን። ትናንት ከሰዓት በኋላ ደወልኩለት፡ እና ዛሬ ጥዋት ደረስን፡ ሁላችንም ያልጠበቅነው ነገር ነው።

6 አሁን አንድ ነገር ባደርግ ጥሩ ይመስለኛል፡ አስቀድሜ፡ አንድ ነገር ግልጽ ባ—ባደርግላችሁ ይሻላል። እኔ፡ ለብዙ ሰዎች፡ በጣም ግራ የሚያጋባ ሰው ነኝ። ለራሴም፡ በራሴ ግራ እጋባለሁ። ምክንያቱም፡ የቻልኩትን ያህል፡ የመንፈስ ቅዱስን አመራር ለመከተል ስለምሞክር ነው። እና ያ ግራ አጋቢዎች ያደርገናል፡ አያችሁ። አንዳንዴ የምናደርጋቸው ነገሮች—ቁጭ ብለን እንድንገረም ያደርጉናል፡ “ለምን እንደዚህ አይነት ነገር አደረግሁ? እንደዚህ አይነት ነገር ማድረግ እንዴት ቻልሁ? ” እና በዚያ ቅጽበት ማድረግ የማይገባ ነገር እንደሰራችሁ ታስቡ ይሆናል። ነገር ግን ብቻ ከታገሳችሁ፡ ካመናችሁም፡ ይህን እንድታደርጉ የመራችሁ እግዚአብሔር መሆኑን እርግጠኛ ከሆናችሁ፡ ሁሉም ነገር በትክክል እንደሚሰራ ትደርሱበታላችሁ። አያችሁ? ብዙ ጊዜ የምናየው ይህንን ነው። እና ወንድም ኔቪል፡ ብዙ ጊዜ ይህ ሆኖ እንዳገኘው አውቃለሁ። መንፈሳዊ መሪዎች እና መንፈሳዊ ሰዎች ይህንን ይረዳሉ።

7 በሕይወቴ ውስጥ የተወሰነ ጊዜ... በእውነቱ፡ ከታናሽነቴ ጀምሮ፡ በጄፈርሰንቪል—ውስጥ እንድኖር ተሰምቶኝ አያውቅም። እዚህ ለመኖር መሞከር፡ ለእኔ ሁሌም የዘይት ውስጥ ዝንብ ይሆንብኛል። በመጀመሪያ ደረጃ፡ የአየር ሁኔታው በጣም ጠላት ይሆንብኛል። ሌላ ነገር ደግሞ፡ የመንፈስ ጭንቀት ያለው ይመስለኛል።

8 እዚህ የሆነ ቦታ ዙርያውን ብትመለከቱት፡ በጎርፉ ወቅት ካልተደመሰሰ በቀር፡ የዚህ ነገር ምክንያት የሚያትት ደብዳቤ፡ ከእኔ ጋር ነበረች፡ ለመጀምሪያ ጊዜ ወደ አገልግሎት በተጠራሁ ጊዜ፡ መሸሽ ጀመርኩ። እና ወንድም ጆርጅ ዴአርክ እና እኔ...

9 እና የወንድም ግሬሃም ስኔሊንግ እናት፡ በኒው አልባኒ የነዳጅ ማደያን የሚያስተዳድረው ወንድም ሃውኪንስ፡ እና ሌሎች ብዙ ሰዎች፡ የጸሎት ስብሰባ ከምንይዝበት ትንሽ ቦታ ውጪ እዚያ አግኝተውኛል። እንዲህም አሉ፡ እዚህ ለመኖር ፍቃደኛ ከሆንኩ፡ ከቦታ ወደ ቦታ ላለመንከራተት፡ ከልጆቻቸውን የምግብ ወጪ ቀ—ቀንሰው፡ ተበርናክሉን ለመስራት እንደሚሞክሩ ይነግሩኝ ነበር።

10 አንድ ሕፃን በእጇ ይዛ ሌላውን በእቅፏ አድርጋ ስለነበረችው፡ ስለ ምስኪኗ እናት ሰስማ፡ የሚያርፉበትና የሚያመልኩበት ቦታ ለመሥራት፡ ከልጆቿን ምግብ ቀንሳ ለመመደብ ተዘጋጅታለች ሲሉ በሰማሁ ጊዜ፡ ይህን መቋቋም አቃተኝ። ስለዚህ እኔና ወንድም ጆርጅ ትንሽ ቆይተን ተበርናክሉን ለመገንባት አብረን ውሳኔ አደረግን።

11 ተበርናክሉ በተሰራ ጊዜም፡ ሁልጊዜ... ተበርናክሉን ባስመረቅሁት ጊዜ፡ ራእይ መጣ፥ ያን ጊዜ በዚያ በመሰረት ድንጋይ ላይ ተቀምጦ ነበር፡ በዚያም መንፈስ ቅዱስ ተናገረኝ፡ “ተበርናክልህ ይህ አይደለም።” አያችሁ? እኔም ተበርናክሌ የት እንደሚገኝ ጠየቅሁት፣ እርሱም በሚያምር ሰማያዊ ሰማይ ስር

አስቀመጠኝ። ከዚያም፡ እናንተም እንደምታውቁት፡ “የወንጌል ሰባኪነትህን ሥራ አድርግ፡” ወዘተ። በመፅሃፍ እንኳን ተፅፏል።

12 እነዚህ ሁሉ አንድ ላይ ተደማመሩ። አንድ ቀን አሁን ወንድም ዉድ በሚኖርበት ግቢ ውስጥ የሣር ሜዳውን እያጨድኩ ሳለሁ፡ በዚያን-ጊዜ-እማቴ በዚያ ትኖር ነበር፥ ከኋላ ባለው ደረጃ ላይ፡ ኮንክሪት ደረጃ ላይ፡ ለእማቴ-በሰራሁላት-ትንሽዬ ቤት ደረጃው ላይ ተቀምጬ ነበርሁ። እርሷም በዚያን ጊዜ የቤተክርስቲያኑ ጽዳት ሰራተኛ ነበረች፡ ታጸዳልን ነበረ። እናም ማንም በግልፅ እንደሚናገር ሰው፡ አንድ ድምጽ ተናገረኝ፡ እንዲህም አለኝ፡ “ከዚህ እስካልወጣህ ድረስ በፍፁም አልባርክህም። ስለዚህም ከህዝብህ ተለይተህ ከዚህ ቦታ ውጣ።” ይህም፡ እኔን፡ ለአንድ ሳምንት ወይም ከዚያ በላይ ለሚጠጋ ጊዜ፡ እጅግ ከፋኝ።

13 ያለማቋረጥ፡ ሁል ጊዜ፡ አንድ ነገር እየመጣ ያሳሰበኛል፡ “ሂድ፡ ሂድ። ወደ ምዕራብ ሂድ። ወደ ምዕራብ መሄድህን ቀጥል።” እንግዲህ፡ እ... ሁሌም እያስቸገረኝ ነበር። እና በእያንዳንዱ ጊዜ እንዲሁ ይመስላል...

14 አሁን፡ በዚህ ሳምንት ወደ ቱክሰን እንደምበር በአእምሮዬ በግልፅ ወሰኜ ነበር፡ ቦታ ለመከራየት፡ ክረምቱን በዚያ ለመሆን፡ ከሴፕቴምበር ጀምሮ፡ ልጆቹን ወደ ትምህርት ቤት ለማስገባት አስቤ ነበር። ቦታውን አግኝቻለሁ። በዚያ የተሰጠኝ ቦታ ሁሉ ነበር። ይሁን እንጂ አንዳች ነገር ይቀራል... እ—እና እኔ ከሄድኩ...

15 ሌላ ማለት የምፈልገው ነገር አለ። ያንን የአገልጋይ መኖሪያ ቤት፡ ከመገንባታችን በፊት፡ አሁን ባለበት ቦታ ላይ፡ ለመስራት አልፈለግኩም ነበር። የባለቤቴ እናት በእድሜ አርጅታ ነበረች። ባለቤቴ በዚህ ጉዳይ ምክንያት አልቅሳ፡ እንዲህ ብላኛለች፡ “እናቴ አሮጊት መሆኗን፡ እና እራሷን መጦር እንደማትችል እያወቅሁ፡ እሷን እዚህ መተው አልችልም።” እንግዲህ፡ ያንን ይገባኛል። ተረዳኋት። እናቷ ነች፡ ያለቻት ወይም የሚኖራት፡ ብቸኛ እናቷ ናት። ስለዚህ፡ ያንን ተረድቻለሁ። ስለዚህ ወ—ወደ ጌታ ጸለይኩ፡ እንዲህ አልኩት፡ “ጌታ ሆይ፡ ይህን ቦታ አልወደውምና፡” እንዲህ አልኩት፡ “እርካታ እንዲሰማኝ አድርገኝ። ከየትኛውም ቦታ፡ ወደምትፈልገው ሁሉ እሄዳለሁ። ነገር ግን ከዚህ አውጥቼ፡ ማንንም ወደማታውቅበት እንግዳ ሀገር ወስጄ፡ ባለቤቴን ማሳዘን አልፈልግም። እንደውም’ኮ፡ እኔ ሁሌም ተጓዥ ነኝ። ብቻ እዚህ ከእሷ ጋር ሆኜ እርካታ እንዲሰማኝ አድርገኝ።”

16 አሁን ደግሞ፡ እናቷ ከተወሰደች፡ ወደ ጌታ ከሄደች በኋላ፡ እንደገና፡ የመሄድ ፍላጎት መጣብኝ፡ እያችሁ። ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም።

17 እናም ደግሞ በቀደም ወንድሞች በየቦታው ይህ አይነቱ ትምህርት መሰፋፋት ሲጀምሩ፡ በባለፈው ለመጨረሻ ጊዜ እዚህ በነበርኩ ጊዜ መድረክ ላይ ቆሜ እነዚህ ነገሮች እስከቀጠሉ ድረስ ወደ ተልዕኮው ወደ መስክ እንደማልወጣ ነግሬአችኋለሁ። ስለዚህ፡ ወንድሞች በሙሉ ልባቸው እነዚያን ነገሮችን ሁሉ አስተካክለዋል። ሁሉም ነገር ጸድቷል። በሃያ-አራት ሰአታት ውስጥ፡ ተጠናቀቀ።

18 ይህም መስኩን እንደገና ከፈተልኝ። ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም። የትኛውን አቅጣጫ እንደምወስድ አላውቅም። ጌታን ራእይ ጠየቅሁት። ምን

ማድረግ እንዳለብኝ እንዲነግረኝ ጠየቅኩት። እሱ ግን እዚያው ቁጭ እንድል አርጎኛል።

19 አሁን፡ ትናንት ማታ ልጆች በሙሉ፡ ባለቤቴን እና ሌሎች ሰዎችን ሁሉ፡ ከቤት፡ ከሸኘኋቸው በኋላ ለጌታ ለእግዚአብሔር ቃል ገብቻለሁ። ጌታ እግዚአብሔርን እንዲህ አልኩት፡ "በምሄድበት መንገድ ብትባርከኝ፡ አገለግልሃለሁ። ግን የት መሄድ እንዳለብኝ፡ እንዴት መቀጠል እንዳለብኝ፡ እና ምን ማድረግ እንዳለብኝ ታሳየኛለህ።" ስለዚህ፡ ራሴን ለጌታ እጅ አደራ ሰጠሁ። አገልግሎቱን እ—እና ሁሉንም ነገር፡ ለጌታ አደራ ሰጠሁት። እኔም፡ "በየትኛውም ቦታ በር ብትከፍት፡ ወይም በምታደርገው ሁሉ፡ በዚያ መንገድ እጓዛለሁ። የማደርገውን እያደረግሁ፡ መንገድ እስክታወጣ ድረስ እጠብቃለሁ።" ያን ጊዜ እንዳልታለል ግልጽ እንዲያደርግልኝ ጠየቅሁት፡ ምክንያቱም አንድ ነገር በሚከሰትበት መሰቀለኛ መንገድ ላይ እንደሆንን በእውነት አምናለሁ።

20 ዛሬ ጠዋት እዚህ በወንድም ኔቪል ሲተነበይ ሰምቻለሁ፡ ወይም እሱ እየተናገረ ያለው—ትንቢት መሆኑን አውቃለሁ። እንግዲያስ፡ እኔ ለሁላችሁ፡ ጸልዬአለሁ፡ ሁላችሁም እንድትጸልዩልኝ እፈልጋለሁ፡ መንፈስ ቅዱስ ወደምሄድበት በትክክል እንዲመራኝ፡ እንዳልሳሳት፡ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ይመራኝ ዘንድ ነው።

21 ምክንያቱም፡ ብዙ ጊዜ፡ ሰዎች ስለ ትንቢታዊ ስጦታ፡ እግዚአብሔር እንዲህ የሚል ይመስላቸዋል "እነሆ **ከዚህ** ወሰጄ፡ **እዚያ** አደርግሃለሁ። አሁንም **ወደዚህ** መንገድ ሂድ።" እርሱ ግን እነዚህን ሁሉ ነገሮች አይነግራችሁም። እሱ እንደዚያ ካደረገ'ማ፡ ታዲያ ምን አይነት አሸናፊ እምነት ይኖራችኋል? አያችሁ? ስለዚህ፡ እናንተ፡ ከማንም በላይ ብቻችሁን እንድትሆኑለት ይፈልጋችኋል። አያችሁ? ሁላችሁም ወደ እኔ መምጣት እና አንዳንድ ነገሮችን ልትጠይቁኝ ትችላላችሁ፡ እስከ ዛሬ ድረሰም መልሱን እየመለሰላችሁ አንድም ቀን ጠብ አላለም። እውነት ነው። አዎን። ነገር ግን ለራሴ ነገሮችን እጠይቀዋለሁ፡ እና ብዙ ጊዜ ዝም ይለኛል፡ አያችሁ፡ ዝም ብዬ እንድቀጥል እና በራሴ እንድገባበት ይተወኛል።

22 አሁን ራሴን መፍታት ያሉብኝ ነገሮች፡ እና ውሳኔዎች ማድረግ ያሉብኝ ነገሮች አሉ። በተለይ ይሄኛው የተናገረኝ እሱ ራሱ መሆኑን እርግጠኛ እስክሆን ድረስ፡ መወሰን የማልችለው ወሳኝ ነገር ነው። እና ራ—ራ... ራዕይ ቢሆንም እንኳ አላሳየኝም። እንዲሁ ዝም ብሎኛል። ስለዚህ ልክ እንደ፡ ወላጅ አልባ ልጅ፡ ዛሬ ጠዋት፡ በ—በየትኛው መንገድ መዞር እንዳለብኝ አላውቅም። ስለዚህ፡ ለጌታ አደራ ሰጥቻለሁ።

23 ይህንን እየተመኘሁ፡ ከ—ከዚያ በኋላ የተሰማኝ ነገር፡ ወደዚህ ተበርናክል ተመልሼ መንገዴ ላይ የሆነ ነገር እስኪሆን ድረስ ወንድም ኔቪልን ልርዳው አልኩኝ። ስለዚህ፡ እብሬ እቆያለሁ።

24 ከትንሽ ጊዜ በፊት "የቤተክርስቲያኑ እድገት እንዴት ነው" በማለት፡ ወንድም ኔቪልን ጠየቅኩት?

እርሱም፡ "ጥሩ ነው" አለኝ።

25 አሁንም በመካከላችሁ የሚሠራ፡ መንፈሳዊ ስጦታዎች እና ነገሮች እንዳላችሁ ስምቻለሁ፡ የትንቢት ስጦታዎች፡ እ—እና በልሳኖች መናገር፡ እና የልሳኖችን መተርጎም፡ ከጥቂት ጊዜ በፊት የሰማነውን ነው። እነዚያም ነገሮች ቤተ ክርስቲያንን የሚያንጹ፡ እና እጅግ የሚጠቅሙ ናቸው።

26 ምናልባት ዛሬ ማታ ግን፡ ወንድም ኔቪል እንዲህ ካደረገ፡ ብዬ አሰብሁ... መንፈስ ቅዱስ በተለያየ ነገር ካልመራን በቀር፡ ዛሬ ማታ እንዲህ ማድረግ እፈልጋለሁ አልኩኝ... ዛሬ ጠዋት፡ ሁላችሁም ከመሄዳችሁ በፊት፡ ጥያቄአችሁ ጽፋችሁ እዚህ ላይ እንድታስቀምጡ፡ ቤተ ክርስቲያን ምን እያሰበች እንደሆነ ለማወቅ፡ በአእምሮአችሁ ውስጥ ያሉ አንዳንድ ጥያቄዎች። ይህ በሰዎች ልብ ውስጥ ያለውን ለማወቅ ፓስተሮች የሚጠቀሙበት መንገድ ነው። ስለዚህ ጥያቄ ያላችሁ ሰዎች ሁላችሁ፡ እዚህ አስቀምጡልኝ። ዛሬ ጥዋት የምታመጡበት—ትንሽዬ ወረቀት ከሌላችሁ፡ ማታ ላይ፡ ቀደም ብላችሁ ጻፉት። ስለዚህ፡ እነዚህን ሁሉ፡ ለመመልከት እና መጽሀፍ ቅዱሳዊ መልስ ለመስጠት፡ የምችለውን ያህል ጊዜ እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ።

27 ከዚያም ጌታ ከፈቀደ፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ፡ ከጥቂት ጊዜ በፊት እዚህ ማስታወቂያውን ተናግሬዋለሁ፡ ስለዚህ በራእይ... የመጨረሻዎቹ ሰባት ማሕተሞች ላይ ልናገራችሁ እፈልጋለሁ። አሁን ምናልባት... በዚህ ዓመት እነዚያን ማኅተሞች መዳሰስ አልቻልኩም፡ ምክንያቱም ከራእይ ምዕራፍ 6 ጀምሮ፡ በ—በእነዚያ ማኅተሞች ውስጥ ለመግባት፡ እስከ 19ኛው ምዕራፍ ድረስ መዳሰስ ይጠይቃል። የመጀመሪያዎቹ ሶስት ወይም አራቱ ግን በአንድ ሌሊት መልስ ሊያገኙ የሚችሉ፡ ይመስለኛል፡ እያንዳንዱ ማህተም አንድ ምሽት ያስፈልገዋል።

28 አሁን፡ ተመልከቱ፡ በራእይ መጽሐፍ ላይ የት እንዳቆምን፡ ከተረዳን፡ ቤተክርስቲያን ወደ ክብር እንደተወሰደች ነው፡ ከዚያም የቀረው ከአይሁድ ጋር የሚሰራው እንጂ፡ ከቤተክርስቲያን ጋር አይደለም። ከአይሁድ ሕዝብ ጋር ነው የሚሰራው ሰራ ነው። ስለዚህ ከቤተክርስቲያን መነጠቅ፡ ወደ ኋላ ወረድ ብለን፡ ማየት አለብን... በእነዚያ ማኅተሞች እና በአህዛብ ቤተክርስቲያን ዘመን፡ ምን እንደሚከሰት እዚህ እናያለን። ቤተክርስቲያን በመሄዷ፥ ስለ እስራኤልን ሕዝብ፡ ትቷቸው ከሄደበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዘመናዊው ዘመን ድረስ፡ መሲሑን እስከሚቀበሉበት፥ እስከ መሲሑ መምጣት ድረስ፡ ወደ ኋላ በመመለስ እስራኤልን ያመጣል።

29 አሁንስ ገባችሁ? ቤተ ክርስቲያን ተወስዳለች። እግዚአብሄርም አስቀድሞ ስራውን ከቤተ ክርስቲያን ጋር፡ በቤተ ክርስቲያን ዘመን ይጨርሳል። ያን አይተነዋል። ከዚያም ቤተክርስቲያን ወደ ክብር ትወሰዳለች። ከዚያም መንፈስ ቅዱስ ተመልሶ እስራኤልን፡ እንደ ሕዝብ ይይዛቸዋል። እናም የሰርጉ እራት በመካሄድ ላይ ሳለ፡ እስከዚህ ድረስ ያደርሳቸዋል፡ ከዚያም በዚያ በመጨረሻ ጊዜ ላይ መልሶ ያመጣቸዋል። እና ጊዜው ሲደርስ፡ ጥቁር ሰሌዳዬን ሰቅዬ፡ ስዕል እየሳልኩ አስተምራለሁ። ከዚያም ጌታ ከሙሽሪት ጋር ይመለሣል፡ እስራኤልም ያዩአታል። ኦህ፡ አቤት፡ ያ ጊዜ እንዴት ይሆን!

30 አሁን፡ ይህንን በደንብ ከማያያዛችን በፊት፡ ለሥነ መለኮት ሊቃውንት እና ለብዙዎች፡ ለዘመናት አስተማሪዎች እና ለክርስቶስ ቤተክርስቲያን ህዝብ፡

እንዲሁም ይህንን ለመስማት የሚመጡትን ሁሉ የሚያደናቅፋቸው ታላቅ ትምህርት አለ፡ ያም፡ የዳንኤል ሰባ ሳምንታት ማለት ነው። እኛ አይተነዋል… ሙሽራይቱን እና እስራኤልን ከዳንኤል ሰባ ሳምንታት ጋር እስክንያይዝ ድረስ በራዕይ ውስጥ ምንም መቀጠል አንችልም። እና ምናልባት፡ እግዚአብሔር ቢፈቅድ፡ ወደ ፊት ቢያናግረኝ፡ ሰባ ሳምንታትን በተመለከተ አንዳንድ ነገሮች እናገራለሁ… ማለቴ፡ ሰባ ሳምንታት ሳይሆን፡ ሰለ ሰባት የመጨረሻዎቹ ማኅተሞች። በሚቀጥለው እሁድ፣ ጌታ ቢፈቅድ፡ በሚቀጥለው እሁድ፡ የዳንኤልን ሰባ ሳምንታትን ለማስተማር እሞክራለሁ። እንግዲህ ያኔ ይህ ይመራናል ከተባለ፡ በሌሎቹ ላይ ለመጀመር፡ መንገዱን ይከፍታል። እና፡ ከዚያ በኋላ እናየዋለን።

31 እኔ እና ወንድም ኔቪል በዚህ ላይ አብረን እንሰራለን፡ አሁንም ለህዝብ ጥቅም የምንችለውን ሁሉ እያደረግን ነው።

32 አሁን፡ በእያንዳንዱ ጊዜ ወደ ኋላ በመመለስ፡ ለታመሙ እንጸልያለን፡ ይህን በማድረጋችን ሁልጊዜ ደስ ይለናል። እና የታመሙ ሰዎች ካሉ፡ ለእነሱ ለመጸለይ፡ ምናልባት በእያንዳንዱ ሰብሰባ ላይ እጸልያለሁ።

33 ከእንግዲህ የመለየት አገልግሎት ማድረግ አልመኻም። አያችሁ፡ የሆነው እንዲህ ነው። እኔም ሞክሬዋለሁ። እና ሰህተት የሆኑ ነገሮችን እንዳደረግሁ አውቃለሁ፥ ይሁን እንጂ ሁሌም ወደ እግዚአብሔር፡ ወደ እግዚአብሔር፡ ለመቅረብ ሞክሬአለሁ፡ እነዚህ ራእዮች የሚመጡብኝ፡ አመጣጣቸው ለዚያ ነው። ዕቃ የጠፋባቸው ሰዎች ሳይቀር፡ ይደውሉልኛል፡ የት እንደጣሉት ለማወቅ፡ በጌታ ፊት ጸልይልኝ ይሉኛል። እሴይ አህዮች እንደጠፉበት፡ እና ብላቴኖቹም ነብዩን ፍለጋ እንደወጡ ሁሉ፡ አህዮቹ ወደ ቤት መመለሣቸው ሁሉ ነገራቸው። እንዲህ የመሳሰሉ ነገሮች፡ ይህ ቢሆንም መልካም ነው። ይሁን እንጂ ብዙ ሰዎች ስለሆኑ፡ እጅግ ይበዛብኛል… እንደዚህ ከአካባቢ ብቻ አይደለም፥ በአለም-አቀፍ ሰረጃ ነው፡ አያችሁ። ሰለዚህ ይህ ነገር፡ እጅግ ያደክመኛል፡ በመቀጠል ከመሰመር እንዳትወጡ ሁል ጊዜ እናንተን መጠበቅ፡ እጅግ እስኪከብደኝ ድረስ ይሆናል…

34 እናም ወንድሞች እኔ በሥጋ የተገለጠው ጌታ ኢየሱስ ክርሰቶሰ መሆኔን የሚገልጽ፡ አሰተምህሮ እንዲጀምሩ ያደረጋቸውም ያ ነው። እናም ያ አገልግሎቱን ሁሉንም እንደሚበጣጠስ፡ እና በክርሰቶሰ እና በሁሉም ነገር ላይ ነቀፋ እንደሚያመጣ እናውቃለን። አያችሁ? ሰለዚህ ወዲያውኑ ለማቆም፡ በታላቅ ድንጋጤ ማሰደንገጥ የነበረብኝ ለዚያ ነው፡ ይህም ከእግዚአብሔር ሳይሆን፡ ከዲያብሎሰም እንደ ሆነ ያውቁ ዘንድ ነው። አያችሁ? ይሁን እንጂ መልካም ሰዎች ናቸው። እነዚያም ሰዎች ከእግዚአብሔር መንፈሰ ዳግመኛ መወለዳቸውን ያሳያል፡ ምክንያቱም፡ እውነቱን በመጽሐፍ ባዩ ጊዜ፡ ወደ እግዚአብሔር፡ በትክክል፡ አያችሁ፡ ወዲያውኑ ተመለሱ። ሰለዚህም፡ ሰይጣን በሰዎች ላይ አንድ ነገር ለማድረግ እየሞከረ መሆኑን ያሳያል፡ ሁሉም ፈሪሃ እግዚአብሄር ያላቸው፡ ክርሰቲያን ሰዎች ነበሩ።

35 ብዙዎችም እንዲህ እንዲሉኝ አድርጓቸዋል፡ “ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ከፊት ይልቅ አሁን ካንተ ጋር እምነት እንዲኖረን አድርጎናል።”

36 ምክንያቱም ተመልከቱ፡ እግዚአብሔር በሰጠኝ፡ በዚህ ስጦታ፡ በዚህ ምን ማድረግ እንደምችል አይታችኋል? አገሪቱን፡ ወይም፡ ህዝቡን በሙሉ ከእግሬ ስር ማድረግ እችል ነበር። **ህዝብ** ብለን የምንለው ነገር፡ "ኮስሞስ" ማለታችን አይደለም፡ ይህ—ሸንተረር እና ሌላ አይደለም። ክርስቲያኖች ማለት ነው፡ እውነተኛው አማኝ፡ ንጥረ ነገሩ ይህ ነው... ስለ **ሕዝብ** ስንሰብክ፡ "ዳግም-ስለተወለደው ህዝብ" መሰበካችን ነው፡ የምንናገረው ነገር፡ ስለ ህዝቡ ነው። እዚህ ውጪ ለተገኘው አቧራ እና ጭቃ፡ በዓለም ሁሉ እየኖረ ላለ ሰው ሁሉ አይደለም፡ ያ'ማ ወደ አፈር መመለሱ የማይቀርለት ተ—ተራ ነገር ነው። እኔ የምናገረው ዳግም ስለ-ተወለዱ ክርስቲያኖች፡ ማለትም እውነተኛ ክርስቲያኖች ስለሆኑ ሰዎች ነው።

37 አንድ ሰው ስለ አንድ ነገር እንደገና እንደሚነቅፈኝ እየጠበቅኩ ነው። አንድ ሰው በቅርቡ ወደ እኔ መጣና፡ እንዲህ አለኝ፡ "ክርስቶስ መሬት ላይ ተፍቶ፡ በምራቁ፡ ጭቃ አድርጎ፡ በሰው አይን ላይ እንዴት ለቀለቀው ብዬ ሳሰብ።" አለኝም፡ "ምራቁን ከአፋ አውጥቶ፡ ሲተፋበት፡ ምንኛ ቆሻሻ፡ አስቀያሚ ነገር ነበር! መሬት ላይ ተፍቶ፡ ጭቃ አብኩቶ በሰው አይን ላይ መለቅለቅ፡ ምንኛ ንጽሕና የጎደለው ነገር ነው።"

እኔም "እርሱ ግን እያየ ተመለሰ፡" አልኩት። አየህ፡ ዋናው ነገሩ ያ ነው።

38 እና ይህ ሰውዬው ራሱ! እዚያ በጎረቤቴ አቅራቢያ ላይ ዕርቃን የሚዋኝበት ገንዳ፡ ታውቃላችሁ፡ መዋኛ ገንዳ ተከፍቷል። እ—እና ይህ ሰውዬ ልጆቹ ሁሉ ወደዚያ ወርደው በዚያ ገንዳ ውስጥ እንዲዋኙ ትኬት ገዛላቸው። እሱና፡ ሚስቱም፡ በዚያ ገንዳ ውስጥ ይሄዳሉ። ይቅርታ፡ እህቶቼ። በዚያ ውስጥ ግን፡ በየቀኑ፡ አንድ መቶ፡ ወይም ሁለት መቶ የሚያህሉ ሴቶች ይዋኛሉ፡ ሴቶች፡ በእርኩሰት እና ክፋት ሁሉ፡ ያውም የዛሬ ሴቶች፡ በውኃው ዙርያ እየታጠቡ፡ ከዚያ ከአፋቸው የሚወጣ ቆሻሻ፡ እየዋጡት ይተፉታል። እንዲነቅፈኝ እፈልገዋለሁ፡ አያችሁ።

39 እነርሱም፡ "ክ—ክርስቶስ ዛሬ በሕይወት ቢኖር ኖሮ፡ ንጽሕና በጎደለው ነገር ይዘው ባሰሩት ነበር።"

40 እሺ **ያኛውስ** ታዲያ? ምን ማለቴ እንደሆነ ተረድታችሁኛል ብዬ አምናለሁ። እዚያ ገንዳ ውስጥ ሁሉም ይገባሉ፡ እና ብዙዎቹ በቂጥኝ፡ በጨብጥ፡ እና በሌሎች ነገሮች ሁሉ፡ ታማሚዎች ናቸው፡ ሁሉም ይገቡበታል። እናም በአፋችሁ ትተፉታላችሁ፡ ወዘተረፈ፡ ከአጠገቡ እንዲህ ትታጠቡበታላችሁ። ድንቄም ንጽሕና ሊባል ነው፡ አይደል?

41 ስለዚህ፡ ኦህ፡ ማይ፡ ወንድም፡ እህቴ ሆይ፡ ዛሬ እየኖርንበት ያለው ዘመን ይህ ነው! ጊዜው የጌታ መምጣት ነው! ቤተክርስቲያንም አንድ ተስፋ አላት፡ ያም የጌታ መምጣት ነው።

42 እንግዲህ፡ እነዚህን ነገሮች እኔ ማስቆም አልችልም፥ ምንም አያስፈልግም። እንደሚመጡ መጽሐፍ ቅዱስ አስቀድሞ ተንብዮአል። እነሱን ማቆም አልችልም። ነገር ግን የፍርዱ ጊዜ ሲደርስ፡ ተቃውሜው እንደነበር፡ ድምፄን በሰማይ እንዲመዘገብልኝ እፈልጋለሁ። ተቃውሜዋለሁና።

43 አሁንም ይህ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ አምናለሁ። ስለዚህ በአለም ላይ የሚገኝ፡ እሱን የሚጻረር ሌላ ነገር በሙሉ፡ በጭራሽ

ሊያስቆመው አይችልም። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ግን፡ ይህ እውነት ነው፡ ይህ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ስለዚህ አሁን መ—መ—መቅዘያችንን እንዘርጋው፡ መልህቃችንንም በእረፍት ውኃ ዘንድ አጠገብ እንጣል። እና—እና ነገ ወደ አንድ ቦታ መጓዝ እንችላለን፡ አሁን ግን መልህቅ እንጣል እና ዛሬ፡ የምንታመንበትን፡ የሰማይ አባታችንን ድምጽ በቃሉ ሲያናግረን አዳምጥ።

44 እናም ዛሬ ማታ፡ አሁን፡ የያዛችሁትን ትንሽ ጥያቄዎቻችሁን አዘጋጁ። አሁን፡ ሰውን የሚጎዳ ነገር አይሁን። ያንን ካደረጋችሁ፡ እንግዲያውስ... ሲጀመር፡ ለእንደዚያ አይነቱ ነገር መልስ አልሰጥበትም፡ አያችሁ። እናንተ ግን፡ **የሆነ-ነገር**፡ የሚባል አይነት፡ "እንግዲህ፡ እኔ፡ እንዲህ እና እንዲያ አድርጌአለሁና፡ እግዚአብሔር ይህን ማድረጋችንን ይፈቅዳልን?" ወይም፡ ታውቃላችሁ፡ በልባችሁ የተቀመጠ ጥያቄ። ወይም፡ "በመካከላችን ጸጋዎች አሉ፡ ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ **በዚህ** እና **በዚያ** መንገድ ልንጠቀምባቸው እንችላለንን? ወይስ፡ ምን እናድርግ?" ከመጽሐፍ ቅዱስ መልስ ልሰጣችሁ የምችላቸው ነገሮች ይሁኑ፡ እሺ። የሆነ ነገር ጻፉ። ደስ ይለኛል። ከሌላ ግን፡ አንድ ርዕስ ጉዳይ በራሴ እመርጣለሁ፡ ጌታ ቢፈቅድም፡ ዛሬ ማታ እሰብካችኋለሁ። ዛሬ እሁድ ነው፡ የነበርኩበትን...

45 ባለፈው እሁድ ወደ ወንድም ካውብል መንገድ ጀመርኩ። እናም የቤተክርስትያን ደወል ሲደወል ሰማሁ፡ እናም በግቢው ውስጥ ወደላይ እና ወደ ታች ተመላለስኩ። ልቋቋመው አልቻልኩም። በቃ። ሰምቻችኋለሁ፡ ስለዚህ እ—እ—እዚህ መውረድ ነበረብኝ።

46 ስለዚህ አሁን አንገታችንን ደፍተን ፈጣሪያችንን፡ በጸሎት ቃል እናነጋግረው። የተለየ የጸሎት ጥያቄ ያለው ሰው አለ? እጆቻችሁን ወደ ላይ አንሡ፡ እንዲህ በሉ፡ "እ..." እንዲታወቅላችሁ አድርጉ። እግዚአብሔር በልባችሁ ያለውን ያውቃል። አሁን ጥያቄአችሁን በአእምሮአችሁ ውስጥ አኑሩት።

47 ሰማያትንና ምድርን በአፍህ ቃል፡ በመንፈስህ አሳብ የፈጠርህ፡ ቅዱሱ እግዚአብሔር ሆይ፡ ስላደረግኸልን ሁሉ እናመሰግንህ ዘንድ፡ በጌታችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ወደ ፊትህ እንቀርባለን። ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ጥዋት፡ ያለንበት አቋም በማወቃችን፡ የቆምንበት ነገር በማወቃችን፡ እና የወቅቱን ታሪክ፡ እና ወደፊት የሚመጣውን ስላወቅን፡ ዛሬ ጠዋት እጅግ እናመሰግናለን። በእግዚአብሔር ቸርነት፡ በቀራንዮ ደም መታጠባችንን፡ ዛሬም እውቀናል። በልባችን ባለው እምነት፡ እርሱን ዛሬ ለመምጣት ከፈለገ እሱን ለመገናኘት፡ እንደተዘጋጀን ዛሬ እናውቃለን። እኛም "አዎን፡ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ና፡" እንላለን።

48 ዓለም በኃጢአት ተጽዕኖ ሥር የምትንገዳገድ እስኪመስል ድረስ፡ ኃጢአቱ ሲከመርባት አይተናል። መጠጥና ቁማር፡ በሰካር መንገዳገድ፡ እና እርቃንነት፡ እና፡ አምላክ ሆይ፡ እርኩሰት፡ እና የሰዎች ቁሽሻ እና ጭቃ ሁሉ እየተደረገ ነው። እነሱም፡ ቢገነዘቡት፡ ጌታ ሆይ! እንደዚህ አይነት ልብስ ለብሰው፡ እንደዚህ አይነት ጨዋነት የጎደለው፡ ተራ ልብስ ይዘው ወደ ጎዳና የሚወጡ፡ እነዚህ ሰዎች ከተራ ትል እና አቧራነት የዘለለ ምንም እንዳይደሉ፡ እጅግ የሚኮፈሱበት ይህ አካል ምናልባት በቀጣይ ሳምንት በታራ ትል ሊበላ እንደሚችል ያውቃሉን? እነዚህ ትሎች እንደሚበሉት ያውቃሉን፡ ነፍሳቸውስ

ለዘለአለም ያለ እግዚአብሔር፡ ያለ ክርስቶስ፡ ያለ ተስፋ በመሆን፡ በመምጣቱ እንዲሁ ለመጥፋት፡ በጥልቅ ሃዘን እንደምትቀር ያውቃሉን? አምላክ ሆይ፡ የማስጠንቀቂያ—ድምፅን ስጠን፡ እያንዳንዷን ነፍስ እየቀረበ ካለው አደጋ እንድናስጠነቅቅ አድርገን።

49 ዛሬ ከእኛ ጋር ሁን። "የጥበብ ቃላት" ስጠን፡ ስሎሞን በአንድ ወቅት በመክብብ እንደተናገረ፡ "ጥበብ ያላቸው እናጺዎች" እንሆን ዘንድ፡ "የዚህ ጉባኤ እረኞች" እንሆን ዘንድ። እኛም ጌታ ሆይ፡ የምንለውን ቃል ስንጠባበቅ፡ እንጸልያለን፡ ዛሬ ጥዋት በጣም የተቸገረውን ልብ—የሚሰቡ ድንቅ ስራዎች እንዲሆኑ እንለምንሃለን።

50 ዛሬ መጥተን በዚህ የሞቀ ጣሪያ ስር፡ እንዲሁ ለታይታ አልተሰበሰብንምና፡ እኛ ግን ወደዚህ የመጣነው ስለምንወድህ፡ እና ካንተ መስማት ስለምንፈልግ ነው። አንተ የምንወደው ፍቅረኛችን ነህ፡ ስለዚህ ከአንተም ቃላትን መስማት እንፈልጋለን። ስለሰማነው ነገር እናመሰግናለን። ከእኛ ጋር ለረጅም ጊዜ ይቆያል። አንተን የበለጠ ስንጠብቅህ፡ ዛሬም ለእኛ የያዝከውን ድርሻ ስጠን። በኢየሱስ ስም፡ ስለ ስሙ እንጠይቃለን። ኣሜን።

51 አሁን እ... [እንዲት እህት በልሳን ተናገረች፡ አንድ ወንድም ተረጎመው—አርታዒ።]

52 ስለነዚህ የመንፈስ ከፍታዎች እናመሰግናለን፡ ምናልባት መንፈስ ቅዱስ ዛሬ ሊናገረን ያለውን ቃል እንድንመለከት ይነግሩናል እና ያስጠነቅቁናልና። እሱ ለእኛ ያዘጋጀውን በትክክል እናውቅም፣ ነገር ግን አንድ ነገር ማምጣቱ እንደማይቀር እናውቃለን። ምናልባት በአእምሮአችሁ ውስጥ ጥያቄ ካለ፡ እሱ በሆነ መልኩ ይመልስላችኋል። በዚህ የጠዋቱ መልእክት ላይ መልስ መስጠት ይችላል። ዛሬ ማታ በአገልግሎት ውስጥ መልስ ሊሰጥ ይችላል። እሱ፡ ዛሬ አንድ ሰው፡ ቃሉን እንዲይዝ፡ ለማስጠንቀቅ እየሞከረ ያለ፡ ይመስላል።

53 እንግዲህ፡ የተጻፈውን ቃል በተመለከተ፡ ለሰንበት ትምህርት ቤታችን የዘጸአትን መጽሐፍ እንመልከት።

54 የጥምቀት ስነ ስርዓት አለባችሁ'ዴ? [ወንድም ኔቪል፡ "የለም፡ ዛሬ ምሽት እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ የለንም" አለ።—አርታዒ።] የለም። ዛሬ ከስአት በኋላ በስድስት ሰዓት የጥምቀት ስነ ስሮኣት ይፈጸማል።

55 አሁን ወደ ዘፀአት ምዕራፍ 17 እንሂድ፡ እና ከ—ከ5ኛው ቁጥር ጀምሮ፡ ይመስለኛል፡ ኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ 17 ላይ 5ኛው እና 6ኛው ቁጥር።

> **እግዚአብሔርም ሙሴን፡ በሕዝቡ ፊት እለፍ፡ ከእስራኤልም ሽማግሌዎች ከአንተ ጋር ውሰድ፥ ወንዙንም የመታህባትን በትር፡ በእጅህ ይዘሃት፡ ሂድ።**
>
> **እነሆ፡ እኔ በዚያ በኮሬብ በዓለት ላይ... በፊትህ እቆማለሁ፥ ዓለቱን... ም ትመታለህ፡ ሕዝቡም ይጠጣ ዘንድ፡ ከእርሱ ውኃ ይወጣል አለው። ሙሴም በእስራኤል ሽማግሌዎች ፊት እንዲሁ አደረገ።**

56 አሁን ይህንን ትንሽ የሰንበት ትምህርት ርዕስ ብጠራው፡ ይህንን የጠዋት ትምህርት፡ **ፍጹም-የማያቋርጥ ከአለቱ የወጣ ውኃ** በሚል ርዕስ እንደ ርዕስ ልወስደው እፈልጋለሁ።

57 እስራኤል የቤተክርስቲያን ታሪካዊ ጥላ እንደመሆኗ እናውቃለን። ምክንያቱም፡ እስራኤል ከግብፅ እስከተለዩ ድረስ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነበሩ፡ በዚያም ከሌላው ዓለም ስለተለዩ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ሆኑ።

58 እኛም ከዓለም ሰንለይ ደግሞ፡ ቤተ ክርስቲያን እንሆናለን። ከሌላው ዓለም ጋር እስከተጣመርን ድረስ ግን፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አይደለንም። አሁን ያ እውነት ጥልቅ እንደሆነ፡ ቦታውንም እንደሚይዝ አምናለሁ። እነሆ፡ እኛም ከዓለም እስክንለያይ ድረስ ቤተ ክርስቲያን አይደለንም። ራሳችንን እንለይ፥ ከአሕዛብም ርኩስ ነገር መካከልም እንውጣ፡ አትደረደሩ፡ ከኃጢአታቸውም አትካፈሉ። ከዓለም ነገር ራሳችሁን ለዩ እንጂ፡ ከማያምኑ ጋር አትጠመዱ።

59 እስራኤልም በግብፅ በነበሩ ጊዜ፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነበሩ። ከዚያም በተጠሩ ጊዜ፡ ወይም በዘጸአት ጉዞ ላይ፡ በወጡ ጊዜ፡ ቤተ ክርስቲያን ተባሉ፡ ምክንያቱም ከዓለም ሁሉ ራሳቸውን የለዩት በዚያን ጊዜ ነበር።

60 **ቸርች** የሚለው ቃልም ትርጉሙ "የተጠሩ" ማለት ነው። **ዘፀአት፡** "መውጣት።" እያንዳንዳችን፡ እንደ ክርስቲያኖች፡ በሕይወታችን ውስጥ ዘጸአት አጋጥሞናል። ከባልደረቦቻችን ተጠርተን የተለየንበት ጊዜ ነበረን፡ በአንድ ወቅት አብረናቸው ከነበሩት ሰዎች መካከል፡ ተጠርተን የተለየ ሕዝብ ሆንን፡ በተለየ መንገድ ከሚናገሩ እና ሰራቸውን በተለየ መንገድ ከሚሰሩ ከተለዩ ሰዎች ጋር ለመጓዝ ተጠርተናል። ይህም በህይወታችን ውስጥ ዘጸአት ነበረ።

61 እስራኤላውያንን እግዚአብሔር በጠራቸው ጊዜ፡ በጣም ጥሩ ምሳሌ ትተውልናል። ዘጸአት አጋጠማቸው፡ ከዓለም አሕዛብ መካከል—ወጥተውም፡ ለእግዚአብሔር፡ የተለየ ህዝብ፡ ልዩ ህዝብ ሆኑ። በምህረት መክደኛው ጥላ ስር ተራመዱ። በታላቁ የእሳት ዓምድ አጠገብ ኖሩ እና ተመላለሱም። እግዚአብሔርም ከግብፅ፡ ወደ ተሰፋው ምድር አወጣቸው።

62 እናም፡ በዚህ በዘጸአት፡ መንፈሳዊ መሪ ሰጣቸው፡ መሪ፡ እርሱም ሙሴ ነበር፡ ታላቅ የተቀባ ነቢይ የሆነው ታ—ታላቅ ሰው። እርሱ እግዚአብሔርን የመሰለ ሰው ነበር፡ እግዚአብሔርን ለመምሰል የተወለደ ሰው ነበረ። እግዚአብሔር ከእናቱ ውስጥ ጠራው፡ ከዚያ ጊዜ በፊትም፡ እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር በፊት፡ ለዚያ ትውልድ መሪ ይሆን ዘንድ ሾመው፡ ይህንን ዘጸአት ለህዝብ ያመጣ ዘንድ መደበው።

63 እዚህ ከተወሰነ ጊዜ በፊት፡ እዚህ በተብርናክሉ ውስጥ ለህጻናት ተናግሬ ነበር፡ እና አንስ ያለች ሰብከት አድርጌላቸው ነበር፥ እና ዮካቤድ እንዴት እንደጸለየች፡ እሷ እና የሙሴ አባት፡ እንበረም እንዴት እንደሆኑ ነገርኳቸው፡ ወይም ትንሽ ምሳሌ ሰጠኋቸው፡ ህዝቡን ሰለማውጣት አንዳች ነገር መደረጉ ነገርኳቸው። እንበረምም የእግዚአብሔርን ራእይ፡ ወይም መልአክ፡ ወደ ሰሜን ሲያመለክት እየና፡ የሚሆነውን ነገረው። ህጻኑ ሙሴም ተወለደ። እነርሱም የንጉሡንም ትእዛዝና፡ ዛቻው አልፈሩም። እግዚአብሔር እጁን በሙሴ ላይ፡ እንዳደረገ አወቁ። በትክክል። ንጉሱ ምንም ቢናገር፡ የፖለቲካው አለም ምንም ቢል፡ ማንም ምንም ይበል፡ እግዚአብሔር በሙሴ ላይ እጁን

እንዳደረገ አውቀው ነበር። ስለዚህ እርሱን በአዞዎች መካከል መጣላቸው፡ አልፈሩም ነበር፥ እነዚያም በሚጥሉላቸው በዕብራውያን ልጆች ሁሉም ወፍረው ነበር፡ ለአዞዎቹ ቀለብ ያደርጓቸው ነበርና። ሙሴ ግን በታናሽ ደንገል ውስጥ ተቀምጦ በአዞዎች መካከል፡ በዚያ በመሃላቸው ተቀምጦ ነበር። ምክንያቱም፡ ምንም ነገር አልፈሩምና፡ እግዚአብሔር በሙሴ ላይ እጁን እንደያዘ አውቀዋልና።

64 እንግዲህ፡ አሁን፡ ያንኑ ነገር፡ ታላቁ መሪያችን፡ መንፈስ ቅዱስ፡ እግዚአብሔር እንደላከው ማወቅ ከቻልን፡ እርሱም መሪያችን መሆኑን ከተረዳን፡ ዓለም ምንም ቢል፡ ምንም ያህል ቢሰቁባችሁ ቢሳለቁባችሁም፡ መሪያችንን እንከተላለን! እግዚአብሔር መሪ ይሆንልን ዘንድ መንፈስ ቅዱስን ላከልን። አያችሁ? "ጥቂት ጊዜ አለ ዓለምም አያየኝም። እናንተ ግን ታዩኛላችሁ፡ ከእናንተ ጋር እሆናለሁና፡ በውስጣችሁም እሆናለሁ፡ እስከ ዓለም ፍጻሜ።" ስለዚህ፡ ታላቁ መሪያችን መንፈስ ቅዱስ፡ ከእኛ ጋር ነው። አሁንም መሪያችንን ተከትለን እሱ እንዳለው ማድረግ አለብን። እና ይህ መሪ ከመንገድ ፈጽሞ አያወጣንም፡ ሁልጊዜም በመጽሐፍ ቅዱስ መንገድ ላይ ይጠብቀናል። **አንዱን** ነገር ፍለጋ ወደዚህ፡ **ሌላውን** ፍለጋ ወደዚያ አይልም። በመጽሐፍ ቅዱሱ መንገድ ላይ የጸና ይሆናል።

65 ሙሴም እስራኤልን የሚመራበት ኮቴ ነበረው፡ እናም በኤርትራ ባሕር በኩል፡ በዮርዳኖስ በኩል፡ በዚያ በምድረ በዳ፡ በቀጥታ ወደ ተሰፋይቱ ምድር ድረስ አለፈ። ከኮቴው ያፈነገጠው ሙሴ አይደለም። ያፈነገጠ አምላክ አልነበረም። ችግርን የፈጠሩት፡ እና ከኮቴው የወጡ እነዚያ ህዝብ ናቸው። ስለዚህ፡ አሁንም ስለ እነዚህ ነገሮች እናስብ። (ይቅርታ አድርጉልኝ።)

66 ሙሴ፡ እንደተቀባ መሪ። በመጨረሻም፡ እግዚአብሔር ብቻ ሊያደርጋቸው በሚችል፡ ምልክትና፡ በድንቅ ለሕዝቡ ከገለጸ በኋላ፡ እነዚህን ምልክቶችና ድንቆች፡ በእስራኤል ሽማግሌዎችና በእስራኤል ፊት አደረገ፡ ይህ ሙሴ ከዚህች አገር ተሰፋ ቃል ወደ ተጋባላቸው ምድር ሊያወጣቸው፡ የተቀባ መሆኑን እስኪያምኑበት ድረስ አደረገ። ከዚያም ሙሴ በእግዚአብሔር ሰም ያደረገውን እነዚህን ታላላቅ ሥራዎች ባዩ ጊዜ፡ እርሱን ለመከተል ፈቃደኞች ሆኑ። እርሱም አወጣቸው፡ በቀይ ባህር መራቸው፡ ወደ ደረቅ ምድር፡ ተሻገሩ፡ ወደ ምድረ በዳ ጉዞ ገቡ፡ ይህ ማለት የፈተና ጊዜ ማለት ነው።

67 አንድ ሰው ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ ሲቀበል፡ ነገር ሁሉ በሰገነት ላይ አለ። ይህ ሰው፡ ወደ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከመድረሱ በፊት ግን፡ ይህ ሰው፡ በመጀመሪያ በመቀደስ ሂደት ማለፍ ይገባዋል። በህይወቱ ውስጥ የፈተና ጊዜ ሊኖረው ይገባል። ሁላችሁም አሳልፋችኋል። ይህን የፈተና ጊዜ አለው። "ወደ እግዚአብሔር የሚመጣ ልጅ ሁሉ፡ አስቀድሞ ይገረፋል፡ ይገሰጻል፡ ይታረማል። ቅጣትን መቋቋም ካልቻልን፡ የእግዚአብሔር ልጆች አለመሆናችንን ያሳያል፥ ዲቃላዎች ነን እንጂ፡ የእግዚአብሔር ልጆች አይደለንም፡" ይላል መጽሐፍ ቅዱስ። ያንን እያወቅን ቅጣቱን ከታገሰን ግን፡ "እግዚአብሔርን ለሚወዱት ነገር ሁሉ ለበጎ ይደረጋል፡" ያን ጊዜ የእግዚአብሔር ወንድ እና ሴቶች ልጆች ነን፡ ከዚያም እስከ ቤዛችን ቀን ድረስ በመንፈስ ቅዱስ ያትመናል። አያችሁ፡ ይህ ሁሉ የምንደርሰበት ቅጣት፡ ጫና፡ የምናልፍበት ነገር ነው።

እስራኤልም፡ እንደ ታሪካዊ ተምሣሌት፡ ይህንን ቅጣት መቀበል ነበረባት።

68 አሁን፡ በግብፅ በነበሩ ጊዜ፡ እግዚአብሔር ሙሴን ላከላቸው። እርሱም ብትሩን ዘረጋት፡ እነሆም ቁንጫና ቅማል ወደ ምድሪቱ መጣ። ወደ ፀሐይም ዘረጋት፡ ጨለመችም። በውኆች ላይ ዘረጋት፡ ደምም ሆኑ። ለምን፡ እስራኤል በከነዓን... ማለቴ—በጌሰም ውስጥ፡ እጅግ ታላቅ ጊዜ ያሳልፉ ነበር፥ ጸሀይ አልጨለመችባቸውም፡ መቅሰፍቱ አልመታቸውም፥ ለምን፡ ታላቅ ጊዜ በማሳለፍ ላይ ነበሩ!

69 ልክ በዳናችሁ ወራት እንደሚሰማችሁ ነገር ነው። ነገር ሁሉ፡ ወፎች ዝማሬአቸው ልዩ ነው፡ ሌላው ሁሉ ደስ ይላል። እና፡ ኦህ፡ ማይ፡ በዳናችሁበት ወራት ላይ ነገር ሁሉ እንዴት ያምራል! ከዚያ በኋላ የፈተና ጊዜ ይመጣል፡ የግሳጼ፡ የመቀደስ ጊዜ፡ ከአለም ነገሮች እራሳችሁን የምትቀድሱበት፡ “ቶሎ የሚከቧችሁን ነገሮች አሰወግዱ።” አንተ፡ ሰው፡ ማጨስህን ማቆም ነበረብህ፡ መጠጣትህን አቆምክ፡ መዋኛ ገንዳ መሄድ ታቆማለህ፡ ልዩ-ልዩ የመሸታ የካርታ ጨዋታዎች ሁሉ። ከእነዚያ ነገሮች ሁሉ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ላይ ባላችሁ እምነት፡ እራሳችሁን ከእነርሱ መቀደስ ነበረባችሁ። እራሳችሁን ትቀድሳላችሁ! እናንተ ሴቶች ፀጉራችሁ እንዲያድግ ታደርጋላችሁ፡ ቀሚሶቻችሁንም ታስረዝማላችሁ፡ በፊት ከነበራችሁት በተለየ መልኩ ትሰራላችሁ። የመቀደስ ወራት! ብዙ ጊዜ ያምፁና ይመለሱ ነበር፥ እንግዲህ፡ ያም የእግዚአብሔር ልጅ አይደለም፡ እያችሁ። የእግዚአብሔር ልጅ በቀጥታ ወደ ቀራንዮ ይመለከታል፡ ይህም ለጥቅሙ እንደሆነ ያውቃል።

70 ስለዚህ የዚያን ወራት ሂደት ውስጥ፡ በእስራኤል ውስጥ፡ ታላቁ ውድቀት የሚመጣው ያኔ ነው። ይህ ታላቅ የሕዝብ-መብዛት ወራት በሆነ ጊዜ፡ ያን ጊዜ ሕዝቡ፡ ከአንዱ ወደ ሌላው መውደቅ ጀመሩ። በዚያም ሲያጉረመርሙ፡ “እንግዲህ፡ ወደ ግብፅ ብንመለስ ይሻለን ነበር። ይህን ቀላል እንጀራ ነፍሳችን ጠላችው።” በሌላ አገላለጽ፡ አሁን ከታሪክ አንጻር ባየው፡ የተናገሩት ያ ነበር።

71 አሁንም በዘመናዊው ጊዜ፡ እንዲህ ይሆናል፡ “ኦህ፡ ዘወትር እሮብ ማታ፡ የጸሎት ሰብሰባ! ዘወትር እሁድ ጥዋት፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን መመለስ! ምን እንሰማለን? ተመሳሳይ ነገር፥ ሰባኪው ተነስቶ ይሰብካል፥ ይዘመራል፥ መመለስ።” እያችሁ፡ ግዴታችሁን ለመወጣት ትሄዳላችሁ። መሰዋዕት አቅራቢዎች አይደላችሁም። መሰዋዕት አቅራቢው መሰዋዕት ለማቅረብ ይሄዳል፡ ይህም በእግዚአብሄር ፊት ራሱን ያፈሳል፡ እግዚአብሔርን ስለ ቸርነቱ ያመሰግናል፥ በእያንዳንዱ ቃል ላይ፡ ይጸናል።

72 ልክ እንደ ፍቅር ግንኙነት ነው። ግዴታህ መሆኑን ስለምታውቅ ብቻ ከሴት ልጅ ጋር የምትሄድ ከሆነ፡ ወይም አንቺም ወጣት ሆነሽ፡ ከወንዱ ጋር የምትሄጂ ከሆንሽ። “እማዬ ከዚህ ወንድ ጋር እንድሄድ ትፈልገኛለች፡ እኔ ግን እሱን አልፈልገውም።” አንቺን ለማየት ይዞት ከሚመጣው አንዳች አታገኚም። ወይም፡ ሴቷም ስለ ወንዱ ያው ነው፡ ወይም ወንዱ ለሴቷ። ከእሷ ትሄዳለህ፡ ትሰለችሃለች፥ እናትህ የምትፈልጋት አይነት ስለሆነች ብቻ እናትህን ከእሷ ጋር እንድትሄድ ትፈልግሃለች። እየህ፡ ያሰለችሃል፥ ፍቅር አይደለም። ግድ አይኖርህም፡ የአንተ ማድረግ አትፈልግም፡ እሷን ለማየት መሄድ አትፈልግም።

ይህም እ… እንዴ፡ አሰቃቂ ነገር ነው። እና አንተን ለማየት በሚመጣበት ጊዜም፡ አቤት፡ ምናለ ቶሎ ቶሎ ቢጨርስ፡ ወደ ቤት በሄድን።

73 እናንተም እንዲሁ ተመሳሳይ ነገር ነው፡ "ይህን ያህል ጊዜ ለምን ይሰብካል? ስለ እነዚህ **ነገሮች**፡ እና ስለ ሌላው ነገርስ?" ኢያችሁ፡ በፍቅር ላይ አይደላችሁም።

74 እያንዳንዷን ቃል በትክክል ስትይዙት ግን፡ መንፈስ ቅዱስ ዛሬ ጠዋት እንዳስጠነቀቃችሁ፡ አያችሁ፡ "በእያንዳንዱ ቃል ላይ ትጸናላችሁ።" እሱ ስለ አንተ ሲናገር የነበረው ይህ ሊሆን ይችላል። ጸንታችሁ ያዙት! የእግዚአብሔር ቃል ሁሉ፡ የዘላለም ሕይወት ነው። በማንኛውም ሁኔታ፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ደስታ ነው። ቢሞቅ፡ ቢበርድ፡ ግድ ባይኖራቸው፡ ህዝብ ሁሉ ቢያጉረመርሙ፡ ቢንጫጩ፡ ምንም ቢያደርጉ፡ የጌታን ቃል መስማት አሁንም ደስታ ነው። ያኔ ከክርስቶስ ጋር ፍቅር አላችሁ፡ አያችሁ፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ትወዳላችሁ።

75 "እነሆ፡ የኔ ማር፡ እሁድ ጥዋት ደረሰች፡ ደግሞ ህጻናትን አጣጥበናቸው ወደዚያ ልንሄድ ነው። ውይ፡ አሰልቺ ነው!" አያችሁ፡ በፍቅሩ አይደላችሁም።

76 ነገር ግን በእውነቱ በፍቅር ላይ ከሆናችሁ፡ እሁድ ጠዋት እስኪመጣ ድረስ አትጠብቁም፡ ከእነሱ ጋር ወደዚያ መውረድ ትናፍቃላችሁ። እኛም ንሄዳለን፡ እና በዚያም… የእግዚአብሔር ሰዎች፡ አይሰለችኋችሁም። ምክንያቱም፡ እነሱ—እህት ወንድሞቻችሁ ናቸው። ድሮ እንደምላችሁ፡ "እንደ ማለዳ የገብስ ሞላሰስ እጅግ ትወፍራላችሁ።" እንዲሁ—አይፈሰምና፡ እንዲሁ ይያያዛል፡ ታውቃላችሁ፡ በደንብ ይተሳሰራል። እንግዲህ፡ ይህ ጥሩ ያይደለ አገላለጽ ነው፡ ይሁን እ—እንጂ—ምን ማለት እንደፈለግሁ ለማሳየት ያህል ነው፡ አያችሁ። አንድ ላይ ተጣመሩ። በቀዘቀዘ ቁጥር፡ በደንብ ይጠባበቃል። እኛም እንዲሁ መሆን አለብን። በቀዘቀዘ…

የምድር ወዳጅ ሲከዳ፡
አብዝቼ ወደሱ እጠጋለሁ!

77 እርስ በርሳችን፡ የምንዋደደው፡ እኛ የተለየ ሰው ስለሆንን አይደለም፥ መውደድ የቻልነው፡ ክርስቶስ በሁላችንም ስላለ ነው፡ አያችሁ። እኛ የወደድነው፡ በማንነታችን ውስጥ ያለውን ክርስቶስን ነው። አሁን አንድ ላይ መሰብሰብ እንወዳለን። የድሮውን መዝሙር እንዘምር ነበር፦

በክርስቶስ ፍቅር ልባችንን
አንድ የሚያደርግ ማሰሪያ ይባረክ፥
የወገኖች የአንድነት ህብረት
ከላይ የሆነው ከሰማይ። (አያችሁ?)

የወገኖች የአንድነት ህብረት
ከላይ የሆነው ከሰማይ።

በአባታችን ዙፋን ፊት፡
ጽኑ ጸሎታችንን እናፈስሳለን፥
ፍርሃታችን፡ ተስፋችን፡ አላማችን አንድ ነው፡
መጽናናታችን እና መሻታችንም እንዲሁ።

78 እያችሁ? አዎን፡ ወዳጄ! አንድ ሰው በረከት ሲቀበል፡ ሁላችንም ደስ ይለናል። አንድ ሰው ሲያዝን፡ ሀዘኑን እናካፍላለን። እኛ—ሁላችንም አንድ ላይ መሆን እንፈልጋለን። እንግዲህ እንደዚህ ነው መሆን ያለብን።

79 እስራኤልም እንደዚያ መሆን ነበረበት። ነገር ግን ሸክም ሆኖበት ነበር፦ “ኦህ፡ ይህ ቀላል ምግብ!” የመላእክት ምግብ፦ “እሺ፡ ስለዚህ ቀላል ምግብ ለምን እንጨነቃለን? ነፍሳችን ይህ ነገር ተጸየፈችው! እና ሁሉም ነገር እየተሳሳተ ነው። እ—እና ይህ የደከመ መና በየምሽቱ የሚወርደው፡ ምነው፡ የግብፃውያን ነጭ ሽንኩርት እና ባሮ ሽንኩርት ይሻለን ነበር።” እያችሁ፡ ልባቸው ለጉዞ ዝግጁ አልነበረም።

80 እና አንድ ወንድ ወይም ሴት ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ ሰላለባቸው ማጉረምረም ሲጀምሩ፡ እና ወደ ቤተክርስትያን መሄድ በጣም ሲሰለቻቸው፡ ለጉዞ ዝግጁ አይደሉም። እውነት ነው። የሆነ ቦታ ላይ የሆነ ችግር አለ።

81 ኦህ፡ እግዚአብሔርን ስትወዱት፡ እና ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመሄድ ስታስቡ፡ ሁላችሁም በአንድነት ትሄዳላችሁ፡

ምን አይነት ህብረት፡ እንዴት ያለ መለኮታዊ ደስታ፡
በዘላለማዊ ክንድ ላይ መደገፍ፡
ኦህ፡ በጌታዬ አጠገብ ልዩ ሰላም፡
በዘላለማዊ ክንድ ላይ ተደግፈን።

እንዴት ያለ... እነዚያን መዝሙሮች እንዘምራለን።

ድካማችንን እንካፈላለን፡
ሸክማችንን ተደጋግፈን፥
ብዙ ጊዜ እርስ በርሳችን
በእንባ እንተዛዘንዛለን።

እንደው ስንለያይ፡
ውስጣችን ያመናል፡
በልባችን ግን አንድ እንሆናለን፡
እና በሚቀጥለው የጸሎት ሰብሰባ ሰዓት ላይ እንደገና
ለመገናኘት ተሰፋ እናደርጋለን። (አዎን፡ ወዳጄ፡አሁንም
በልባችን አንድ!)

82 አሁን ለጉዞ እየተዘጋጀህ ነው፡ ተመልከት፡ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት ተዘጋጅተሃል። የፈተናው ወራት፡ አደገኛ ክልል አለ፥ በረሃው፡ የፈተናው ወራት።

83 እስራኤል፡ በፈተናቸው ወራት፡ እርስ በርስ መጨቃጨቅ፡ እና ምግብ መጥላት ጀመሩ። ወደ ግብፅም መመለስ ፈለጉ።

84 እናም በዚያ ስለ መሪያቸው ማጉረምረም ጀመሩ። ኦህ፡ እርሱ ከትክክለኛው ምሪት እየመራቸው እንደሆነ ፈሩ፡ ይህም መሪ መሆኑን ካሳየ በኋላ፡ እግዚአብሔርም መሪ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ። “ይኸውላችሁ፡ ምናልባት ትንሽ ከአክራሪነት አብዝተን ነው። እናም—እና ምናልባት ሰተናል፡ በተሳሳተ መንገድ፡” ወይም፡ እንደዚህ ያለ ነገር፡ እነሆ፡ በእግዚአብሔር እና በሙሴ፡ በእግዚአብሔር እና በመሪው ላይ ይናገሩ ነበር።

85 እንግዲህ፡ እንዲህ ወደምንልበት ሁኔታ ስንደርስ፡ “ቃሉ **ይህ** ማለት እንደሆነ፡ ወይም እንዳልሆነ አላውቅም፡” እና፡ “ስለ መንፈስ ቅዱስም አላውቅም፥ በዚህ ጉዳይ ላይ ትንሽ ጥርጣሬ አለብኝ። የሌላቸውን እንዳሉ አውቃለሁ።” እንግዲህ፡ ወደ ግብፅ ሂዱ። እያችሁ?

86 በእውነት በመንገድ ላይ ለመቀጠል ከቆረጣችሁ ግን፡ ያንን መሪ መንፈስ ቅዱስን፡ አጥብቀህ ያዝ፡ በቃሉ ላይ አጥብቀህ ያዝ። በመንፈስም ብትኖር፡ እርሱ በቃሉ ይጠብቅሃል። እውነት ነው። እርሱ በቀጥታ መንገድ ላይ፡ በቃሉ መንገድ ይመራችኋል። እሱን አትፍሩ። አይጎዳችሁም፡ ስትጎዱ የሚጠቅማችሁ ብቻ ነው። ህመማችሁን ሁሉ ይፈውሳል፡ መንፈስ ቅዱስ ይህን ያደርጋል።

87 አሁን እንደተመለከትነው፡ በጉዞ ላይ ሳሉ፡ እንደዚህ ወዳለው ሁኔታ ከገቡ በኋላ፡ ኮሬብ ወደተባለው ስፍራ እንደደረሱ እናያለን። እና H-o-r-e-b፡ ኮሬብ ላይ፡ አንድ ነገር እናያለን... ያንን ስም እንመርምረው። **ኮሬብ** የሚለው—ስም “ደረቅ ቦታ” ወይም “በረሃ” ማለት ነው።

88 እናም በቤተክርስትያን ውስጥ እርስ በርሳችን ህብረት ማድረግ ስናቆም፡ እና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ህብረት ከተውን፡ ወደ ደረቅ ምድር ያመጣናል፡ ምንም ወደሌለበት፡ ወደ ምድረ ባዳ ይወስደናል፡ በዚያም ነገር ሁሉ በእሾህ የተሞላ ነው። እያችሁ፡ በ—በረሃ፡ በእሾህ የተሞላ ትንሽ ቁልቋል ያለበት። ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ምንም ውሃ ሳታገኝ የቀረች ውድ የሆነች ትንሽ ለሰላሳ ቅጠል ነው፡ እሾህ እስኪሆን ድረስ በራሷ ላይ ተጠምጥማለች። እና እንደዚህ አይነት ሰው ስታዩ፡ ምናልባት ጥሩ ውሃ ጠጥታ ቢሆን ኖሮ ትንሽ ትንሽ ቅጠል ወይም ሌላ ነገር የሆነች ውድ ነፍስ ነች። ለሰላሳ ትንሽ ቅጠል ወይም ሌላ ነገር ሊሆን ይችል ነበር። ነገር ግን በዛ ፈንታ፡ እሾህ እስኪሆን ድረስ እራሱን ይወጋጋል፡ ሁሉንም ይወጋጋል፡ ታውቃላችሁ፡ ስሕተት ፈላጊ ይሆናል። የሚያስፈልገው ውሃ ብቻ ነው። ይኼው ነው። እሱ ብቻ ነው የሚያስፈልገው—ሪቫይቫል፡ ወይም መፈራረስ፡ ከጌታ የሆነ መንፈስን የሚያድስ ነገር። ውኃ ውስጥ ካስገባችሁት፡ ያ—ያኔ ትንሿ ማንነቱን መብቀል ትጀምራለች።

89 ነገር ግን፡ በእንደዚህ አይነት አካባቢ የሚኖሩት፡ የዚያን አካባቢ ሁኔታዎች መቋቋም አለባቸው። እና ሁሉም ነገር በቡጢ እና በጫጫታ በሆነበት፡ በእንደዚህ ዓይነት ድባብ ውስጥ ለመኖር የሚፈልጉ፡ በመጨቃጨቅ እና በእንደዚያ አይነት መቆሳሰል፡ እንግዲያውስ፡ በዚያን አይነት ድባብ መኖራችሁ ግድ ነው፡ በቃ። በዚያ ውስጥ መኖር ግን የለብንም፡ እዚያ መቆየታችን አስፈላጊ አይደለም።

90 ስለዚህ፡ ይህ ኮሬብ የሚባል ቦታ እግዚአብሔር በሕዝቡ ተስፋ የቆረጠበት ስፍራ ነው፡ ምክንያቱም ወደዚህ ቦታ ተቅበዝብዘው በዚህ ድባብ ውስጥ ገብተው ነበርና። በመንገዱም መሄድ ስላልፈለጉ፡ እርሱም ወደዚያ መራቸው። ዋናውን—መንገድ ትተው፡ የዳር መንገዱን ይዘው ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር አንድ አስፈሪ ነገር እንዲሠራ አደረገው። እርሱ... እግዚአብሔር ሙሴን በአገሪቱ ላይ የፈረደበትን የፍርድ በትር እንዲይዝ፡ ዓለቱንም እንዲመታ፡ ከእርሱም ውኃ እንዲያወጣ እንዲነግረው አስገደደው።

91 አሁን፡ በቀላሉ መረዳት ከቻልን ይህ የሚያምር ትምህርት አለው፡ እያችሁ። እኛም ከመስመር እጅግ በመውጣታችን ምክንያት፡ በዓለም ነገሮች

በመታጠራችን፡ እና በሌሎች፡ እግዚአብሔር የዓለምን ፍርድ ወሰዶ እኛ ነጻ እንሆን ዘንድ፡ የገዛ ልጁን፡ በቀራንዮ ይመታ ዘንድ ተገደደ። ምን ማለቴ እንደሆነ እያችሁ?

92 አሁን፡ እነዚህን ሰዎች ወደ ውኃ ለማድረስ፡ እዚያ ከደረሱ በኋላ፡ ይህ ደረቅ ቦታ ቀራንዮ ሆነ። በዚያም፡ እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ አለው፡ "በትሩንና ሽማግሌዎችን ይዘህ፡ ውጣ፡ እኔም በፊትህ በዓለት ላይ እቆማለሁ።" ይህም ዓለት ክርስቶስ ነበር። ሙሴም፡ በእስራኤል ሕዝብ ላይ ፍርድ ባመጣባት በትር፡ ይህንኑ በትር ወሰዶ የእግዚአብሔርን ፍርድ በዓለቱ ላይ አወረደ። እያችሁ? የህዝቡን ኃጢአት ወደዚህ በትር ወሰደ። ይህም፡ ህዝቡን መምታት ነበረበት። ቢሆንም ህዝቡን ከመምታት ይልቅ፡ አለቱን መታ። ዓለቱም፡ በእግዚአብሔር አሰራር፡ መዳንን አመጣ፡ ለሚጠፋውም ሕዝብ ውኃ አመጣ። እየሞተ ላለው ሕዝብ ሕይወትን አመጣ። እግዚአብሔርም የ—የፍርዱን ዘንግ በመያዝ ያደረገው ይህ ነው፡ እና ኃጢአቶቼን እና ኃጢአቶቻችሁን በዚህ በትር ዙሪያ ጠመጠመው፥ እኛን ሊመታን ሲገባው፡ ክርስቶስን መታው፥ ከእርሱ ዘንድም **ውኃዎች** ፈለቁ፡ ይህ ማለት "መንፈስ" ነው፡ ሕይወትን ሊሰጠን፡ መንፈስ ቅዱስ ከእርሱ ወጣ። አሁን የዘላለም ሕይወት አለን። አሁን፡ ያ ዓለት ክርስቶስ ነበር። አሁን በደንብ እናስተውል።

93 የዚህን ዓለት በጣም ብዙ ምሁራዊ ቅጂዎችን አይቻለሁ። ካየሁት በጣም ከሚያስደንቁት አንዱ፡ በቅርብ ጊዜ ነው፡ አንድ ትንሽ አ—አለት በኮረብታ ላይ እስከ ማስቀመጥ ድረስ ደርሰዋል። እናም—እና ሙሴ ያንን አለት በመታ ጊዜ፡ ከዚያ አለት የሚንጠባጠበውን የውሃ ጠብታዎች ለመቅዳት እስራኤላውያን የሻይ ኩባያ ይዘው ከታች ቆመው ነበር። እንግዲህ ይህ የአንድ ግለሰብ አስተያየት ብቻ ነው።

94 ነገር ግን ይህ ዓለት ውኃውን ባወጣ ጊዜ ግን፡ ከበሬዎች፡ ከግመሎችና፡ በገንዳው ውስጥ ከሚጠጡት ሁሉ ሌላ፡ ከሁለት ሚሊዮን በላይ ሰዎች ነበሩ። ከዚያ የወጣው ታላቅ ጅረት ነበርና!

95 ዛሬ ክርስቶስን፡ መንፈስ ቅዱስን ለመሳል የሚሞክሩት በዚህ መንገድ ነው። "ትንሽ መረጨት ብቻ ያደርጉታል።" እያችሁ፡ እምላክ እንዳለ እንድታምን የሚያደርግ በቂ ነገር ብቻ። አይ።

96 የተትረፈረፈ ውሃ ነው! ዳዊት እንዲህ አለ፡ "ጽዋዬ የተትረፈረፈ ነው!" የመንፈስ ቅዱስ ጅረት ነው።

97 ሰዎች ይፈሩታል። አንዳንድ ሰዎች፡ "እንግዲህ፡ **ይህን** ወይም **ያንን** እንዳደርግ ትንሽ እፈራለሁ፡ ወይም ትንሽ ወደ ጠለቅ ብዬ ብሄድ። ትንሽ በጣም ርቆ የገባ ሰው ላሳያችሁ እችላለሁ።" በበቂ ሁኔታ ያልሄደውን ሰው ግን በጭራሽ አይጠቁሙም። እያችሁ? አዎን፡ በቂ ርቀት ያልዘለቁቱስ?

98 አሁን፡ ወደ ሥጋ የገቡ፡ እና በተሳሳተ አካሄድ የወጡ አንዳንድ ሰዎች ይኖራሉ። እና—ሕዝቡ እንጂ፡ እግዚአብሔር አይደለም... ጥሩ አመራር ባለመኖሩ፡ ወዘተ፡ ሌሎችም በተሳሳተ አካሄድ አውርደው፡ ወደ አክራሪነት ይገባሉ። ያን ጊዜ መላው ዓለም፡ ዲያብሎስ ይጠቁምባቸዋል፡ "ይኸው እዩት! ይኸው እዩት!"

99 እንግዲህ፡ ዛሬ ጠዋት እዚህ ቆሜ ስለእነዚህ በአሰር ሚሊዮኖች የሚቆጠሩት ገና እንኳን ጅምር ላይ ያልደረሱትን ልናገር። ስለ እነርሱስ? እያችሁ፡ ሁኔታቸውን ተመልከቱ። ዛሬ እንደ ኢችማን ያለ ሰው ተመልከቱት፡ ምን ያህል… "ጴንጤዎች ሰነምግባርና ጨዋነት የጎደላቸው፡ መሃይሞች ናቸው፡" እና የመሳሰሉት፡ ይላሉ። በዓለም ላይ ካሉት፡ በጣም የተማሩ ሰዎች አንዱ የሆነውን ኢችማንን ተመልከቱት። ሰድሰት ሚሊዮን፡ ሕፃናትን ሴቶችንና ወንዶችን፡ ሰድሰት ሚሊዮን ነፍሳትን ገድሏል። ወደ እንደዚህ አይነት ሰው መጠቆም ትፈራላችሁ።

100 ነገር ግን፡ በጭራሽ ማንበብ ወደ ማይችል አንድ ምስኪን ሰው፡ ምናልባት የመጽሐፍ ቅዱስን ሰም በተሳሳተ መንገድ የሚጠራ፡ ወይም፡ የሆነ ነገር በስህተት የሚናገር ወይም የሚሳሳት፡ ወይም ሰህተት ከሠራ፡ ጋዜጦች ያንን በየቦታው መለጠፍ ይፈልጋሉ፡ እና "ታማኞች አይደሉም፡" በማለት ይናገራሉ።

101 ታዲያ ያ የማይታመን ከሆነ፡ ታዲያ ትምህርትስ፡ ዛሬ ያሏቸው ነገሮች እና ሙሁራን ያላቸው ነገርስ? አዶልፍ ሂትለርን ተመልከቱት። ዛሬ የዓለምን አእምሮ ተመልከቱት። ተመልከቷቸው። ድሮ ሲተርሰቱ "የወንዱ ዝይ መረቅ ለሴት ዝይም እንዲሁ ነው፡" ይሉ ነበር።

102 ማድረግ ያለባችሁ ነገር፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ትክክል እና ሰህተት የሆነውን መለየት፡ ትክክል የሆነውን እና ሰህተት ማወቅ መቻል ነው።

103 አሁን፡ ይህ የነበራቸውን ቀራንዮን አይተናል፡ እንዲሁ ስለ ህዝቡ የወረደው የሕይወት ውኃ ጅረት ጭምር።

104 አሁን፡ አንዳንድ ሰዎች በልባቸው እና አእምሮአቸው እንዲህ ያሰባሉ፡ እሰራኤል ሁሉ ከጠጡ በኋላ፡ ግመሎቻቸው ጭነው ፈረሶቻቸውንና ሁሉ እና ጓዛቸውን ጠቅልለው፡ ወዘተ፡ ያንን የሚንጠባጠብ፡ አለት በዚያ ትተው፡ ልጆቻቸውንም ይዘው ወደ ሌላ ቦታ የሄዱ አርገው ያሰባሉ። ይህ ሰህተት ነው።

105 ይህ ዓለት ተከተላቸው፡ ይህም ውኃ ተከተላቸው። እንግዲህ በ1ኛ ቆሮንቶስ፡ ይመስለኛል፡ በምዕራፍ 10 ላይ፡ ከቁጥር 11፡ ታገኙታላችሁ፡ ያም "አለቱ እሰራኤልን እንደተከተላቸው ነው።" ከዚያን ቀን ጀምሮ በሄዱበትም ሰፍራ ሁሉ፡ ዓለቱ ከእነርሱ ጋር ሄደ፡ ውኆችም ተከተሏቸው።

106 እንዴት ያለ ቆንጆ ጥላ ነው፡ ለዚህ ዘመን አማኞች እ—እንዴት ያለ ድንቅ ድጋፍና መልሕቅ ነው፡ ማለት ይህ አንዴ የተመታው አለት፡ ይህ ከቀራኒዮ አንድ ጊዜ የፈሰሰው ውሃ፡ የትም ከኛ ጋር ይሄዳል! ኦህ፡ ማይ! "እሺ፡ ከትናንት በሰቲያ፡ እዚያ ውሃ ነበረን፡" በማለት፡ ወደ አንድ ቦታ መመለስ አይደለም። ዛሬም፡ እዚሁ ውሃ አለን፡ ምክንያቱም ያ አለት ክርሰቶሰ ነበረ! ክርሰቶሰም ትናንትና፡ ዛሬም፡ ለዘላለምም ያው ነው።

107 እያችሁ፡ ይህ ዓለት እሰራኤልን ተከተለ። ዓለቱን የተከተሉት እነሱ አይደሉም፡ የተከተላቸው ዓለቱ ግን ነው። ኣሜን። እሰራኤል ጉዟቸውን ቀጠሉ። አንድ ነገር ብቻ ማድረግ ነበረባቸው፡ ይኸውም፡ ቀጥተኛውን መንገድ ይዞ መጓዝ ነው፡ በቀጥታ ወደ ተሰፋይቱ መንገድ መጓዝ። ዓለቱና ውኃውም ተከተሉአቸው።

… **አለቱ** ተከተላ**ቸው**፡…

1ኛ ቆሮንቶስ፡ ምእራፍ 10 በደንብ ይነግራችኋል፡ በጣም ጥሩ።

… **ያም አለት ክርስቶስ ነበር።**

108 እግዚአብሔር የሰዎችን ፍርድ ወሰዶ በክርስቶስ ላይ አኖረው፡ እርሱንም መታው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ፡ በአለቱ ውስጥ ሰንጥቅ እንደነበረ፡ አስተውላችኋል? አለቱ በውስጡ፡ ሙሴ የመታው ሰንጥቅ ነበረው። ክርስቶስም በተመታ ጊዜ፡ ሰንጥቅ ነበረበት፡ “ስለ ኃጢአታችን ቈሰለ፡ በእርሱም ቊስል እኛ ተፈወስን።” ከዚያ ሕይወት ዛሬ በጣም የምንባረክበትን የሕይወት ውሃ መጣ!

109 አሁን፡ ይህን ህይወት ማግኘት እንድትችል፡ የክርስቶስ ህይወት ከቤተክርስቲያን ጋር እንዳለ፡ አስታውሱ። ሃሌሉያ! ኦህ፡ በሚቀጥሉት አስር ደቂቃዎች ላይ ሀሳባችንን በዚያ ላይ እናድርግ! ክርስቶስ ከቤተክርስቲያንን አይወጣም። “እስከ ዓለም ፍጻሜም ቢሆን፡ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ።” ክርስቶስን የሚተው ሰዎች እንጂ፡ ክርስቶስ ሰዎችን አይተውም። ሰዎች ባለማመናቸው፡ ይተውታል። እነሱ ክርስቶስን ትተውታል እንጂ፡ ክርስቶስ ሰዎችን አልተወም።

110 እስራኤል ከምንጩ ወጣ እንጂ፡ ምንጩ ከእስራኤል አልወጣም። አያችሁ? መጽሐፍ ቅዱስም በግልጥ፡ “አለቱና ውኃው እስራኤልን ተከተሉ፡” ይላልና። ይከተሏቸው ነበር! የትም ቢሄዱ፡ እሱ ደግሞ፡ ይሄዳል።

111 ኦህ፡ ዛሬ ጥዋት፡ ጊዜ ቢኖረን፡ ወደ ኢያሱ 1ኛ ምዕራፍ፡ ብናየው ደስ ይለኛል፡ እንዲህ ብሎ የሚናገርበት ክፍል፡ “የእግርራችሁ ጫማ በሚረግጥበት ሁሉ፡ እኔ ሰጥቼሃለሁ። በምትሄድበት ሁሉ፡ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው። ማንንም ሰው አትፍሩ። አይዞህ! እግርህ የረገጠው ስፍራ ሁሉ፡ የትም ቢሆን፡ በዚያ እገኛለሁ።” እግዚአብሔር ከኢያሱ ጋር ሄዷል!

112 ያው እግዚአብሔር ዛሬ ጠዋት ከቤተክርስቲያኑ ጋር ይሄዳል። እኛም ከዚህ ምንጭ እንጠጣ። የትም ቦታ ብትሄድ፡ ውሃና ሕይወት ሊሰጥህ፡ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሆናል። “እነሆ እስከ አለም ፍጻሜም ድረስ፡ እኔ ሁል ጊዜ ከአንተ ጋር እሆናለሁ።” ክርስቶስ ትናንትም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለምም ያው ነው። የእግዚአብሔር ህግጋት።

113 እናንተም፡ “እንግዲያውስ፡ ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ታዲያ ማድረግ ያለብንን ነገሮች የማናደርገው ለምንድን ነው? በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት ስጦታዎቻችን እና ነገሮች፡ መሆን ወዳለባቸው ወደ ውበታቸው ለምን አይመጡም? ቤተ ክርስቲያናችን መገኘት ወዳለባት ከፍታ የማትወጣው ለምንድነው? ” ሰሰዎቹ፡ በፈተናቸው ወራት፡ ልክ እንደ እስራኤል ሰለወደቁ ነው። አምላክ የተዋቸው ይመስላቸዋል።

114 ነገር ግን፡ አስታውስ፡ አለቱ ከእስራኤል ርቆ አያውቅም። እስራኤላውያን አለቱን ትተው ወጡ፡ ዓለቱ ሁል ጊዜ አብሯቸው መሆኑን ረሱ። እሱ አጠገባቸው ነበረ፡ እስከ መንገድ ፍጻሜ ድረስ አብሮ ነበረ። “ተከተላቸው።” ከእነርሱ ጋር በማይነጋገርበት ርቀት አልነበረም። እነርሱን በማይሰማበት ርቀት አልነበረም። ወይም፡ እነርሱን ማየት በማይችልበት ርቀት አልነበረም።

115 ክርስቶስም እንዲሁ ነው! ዛሬ ከቤተክርስቲያን፡ እሱ ከመናገር ርቀት አልወጣም። አንዳንዶቻችሁ ወደ ኋላ ብላችኋል፡ ስህተት የሆነውን ነገር አድርጋችኋል፡ ያንን ደስታም አጥታችኋል፡ ውሃችሁ ደርቋል። እሱ አሁንም ከእናንተ ጋር በንግግር ርቀት ላይ ይገኛል። ይከተላችኋል። የምታደርጉትን እንቅስቃሴ እና የምታደርጉትን ሁሉ ያውቃል። በቦታው ላይ እሱን ስትጠሩት ለመስማት ይጓጓል።

116 እናም ይህ ታላቅ የጴንጤቆስጤ እንቅስቃሴ ዛሬ፡ እግዚአብሔር በቦታው ላይ እንድትጠሩት እየጠበቃችሁ ነው። ከእርሱ ከንግግር ርቀት ወጥታችሁ አልራቃችሁም። ብናጠፋም፡ ብንበድልም፡ ጀርባችንንም ብንመልስለትም እንኳ፡ ል—ልናደርገው የማይገባውን ብናደርግም፡ እርሱ ግን ከእኛ ጋር ነው። ክርስቶስ ከእኛ ጋር እንደሚሆን ተናግሯል።

117 መጽሐፍ ቅዱስ "ውሃው የእስራኤልን ልጆች እንደተከተለ፡" ይናገራልና። በተጠሙ ጊዜ፡ ውሃው ቅርብ እንደነበረ ያውቃሉ።

118 አሁን፡ እነዚህ ነገሮች በህግ ስር የሚከናሰወኑ ናቸው። የእግዚአብሔር ሥርዓት ሁሉ በሕግ የተደነገገ ነው። ለምሳሌ እንወስዳለን… ለአንድ ደቂቃ ያህል እናቁም።

119 ዓለምን እንውሰድ። በየሃያ-አራት ሰአታት ውስጥ፡ ሁለት ፍጹም የሆኑ ዑደቶችን፡ ትሽከረከራለች፡ በዚህም… በደረስንበት ሳይንሳችን ሁሉ፡ ትክክለኛውን ጊዜ የሚገልጽ ሰዓት መስራት፡ በፍጹም አልቻልንም። ከብዙ ጊዜ አንዴ፡ ምርጥ የተባሉ ሰዓቶች እንኳን በአንድ ዓመት ውስጥ፡ ብዙ ደቂቃዎች ያልፋሉ፡ ወይም ወደኋላ ይቀራሉ። አለም ግን አትወድቅም በሴኮንዷ ላይ ትደርሳለች። ዛሬ ሳይንቲስቶች፡ እና የሥነ ፈለክ ተመራማሪዎች ሁሉ፡ ፀሐይና ጨረቃ በሃያ ዓመታት ውስጥ ወይም በሃምሳ ዓመታት ውስጥ፡ አንዳቸው በአንዳቸው ላይ መቼ እንደሚተላለፉ በትክክል ያስቀምጣሉ። በሃያ-አራት ሰዓት ዑደቱ ውስጥ ስትዞር፡ እንዲሁም በአንድ ወቅት በምህዋርዋ ስትመለስ፡ አንዲት ሴኮንድ ወደ ኋላ አትልም። ሃሌሉያ! እንደ እግዚአብሔር ሕግ ስለምትሠራ፡ ፍጹም ናት።

120 ማዕበሉ መቼ እንደሚነሣ፡ ደቂቃውን ሳይቀር በትክክል ያውቃሉ፡ ምክንያቱም ጨረቃ በየትኛው ወቅት እንደምትጠልቅ ያውቃሉ። እግዚአብሔርም ሁሉን በሕግ አጸናው። እና ጨረቃ ስትጠልቅ፡ ማዕበሉ አብሮ ይጠልቃል። ጨረቃ ስትወጣ፡ ማዕበሉ በተመሳሳይ ጊዜ አብሮ ይወጣል። እና በጊዜ አቆጣጠር፡ ጨረቃ መቼ እንደምትጠልቅ፡ በትክክል ያውቃሉ። ከዓመታት በፊት በአልማናክ ካላንደር ውስጥ ሊያስቀምጡት ይችላሉ፡ ማዕበሉ መቼ እንደሚወርድ፡ ደቂቃውን ሳይቀር ሊነግሯችሁ ይችላሉ። በትክክል፡ ምክንያቱም ጨረቃ የምትወጣው በዚህ መንገድ ነው፡ ምክንያቱም በእግዚአብሔር ህግ ቅደም ተከተል ላይ ስለተዘጋጀ ነው።

121 ባለፈው ቀን፡ በሚቺጋን ሀይቅ አጠገብ፡ ቆሜ ነበር። እናም ወደ ካናዳ በሚወሰደው መንገድ ላይ፡ ወደዚያ ትልቅ የውሃ አካል፡ ወደሚገኘው ሱፐሪየር ሀይቅ ሄድኩ። በዚያ ቆሜ፡ "ይህ ትልቅ የውሃ አካል ስንት ማይል የውኃ ይዘት ይሆናል፡" ብዬ አሰብኩ? እና ያንን ሚቺጋንን-… ፡ ወይም፡ ሱፐርየር ሃይቅን ከተሻገርኩ በኋላ፡ ሚቺጋን እስክደርስ ድረስ፡ እኩል የውሃ አካል አለው። እና

ወደዚያ ለመሄድ፡ ከሱፐርየር ሃይቅ እስከ ሚቺጋን ሀይቅ፡ ከሚቺጋን ሀይቅ እስከ ኦንታሪዮ ሀይቅ ድረስ፡ እና እስከ... ሁሮን ሀይቅ፡ እና እነዚያ ሁሉ ሀይቆች አንድ ላይ። በእነዚህ ሐይቆች ውስጥ ምን ያህል ቢሊዮን ቢሊዮኖች ቢሊዮኖች በርሜል፡ የማይቆጠር ንጹህ ውሃ ይገኛል!

122 እና በኔቫዳ፡ በአሪዞና፡ በኒው ሜክሲኮ፡ በምስራቅ ካሊፎርኒያ፡ በሚሊዮን የሚቆጠር ሄክታር መሬት፡ የደረቀ በፀሐይ የተቃጠለ መሬት አለ። እነዚህ መሬቶች ለም በመሆናቸው፡ ይህ ውሃ ወደ እነዚህ አገሮች ቢደርስ፡ ይህች አገር ትርፍራፊውን ወደ ባህር እየተጣለች፡ ማንም ሳይራብ፡ ዓለምን ሁሉ ልትመግብ ትችላለች። በትክክል! በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሄክታር ቶን እና በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ቶን ድንቾች፡ እና ጎመን እና ባቄላ እ—እና ሰላጣ፡ ራዲሽና ሴሊሪ፡ ኩኮምበር፡ እና ሌሎች ማብቀል ትችላለች። መሬቱ ማብቀል በቻለ ነበር፡ ና—ናፍቆቱ ሁሉ ውኃ ብቻ ነው።

123 እንግዲህ ውሃው **እዚህ** አለ፡ መሬቱም **እዚህ** አለ። ይኸው እንደምናየው፡ እንደሚቻል እናውቃለውን፡ ምክንያቱም ውኃው ሲፈተሽ ፍሬሽ ነው፡ አፈሩ ሲመረመርም ለም ነው። አሁን፡ ምኞቶቻችን ሁሉ፡ ይህን አያደርጉልንም። ይሁን እንጂ፡ አንድ ሕግ አለ፡ ይህም የሰበት ሕግ ይባላል። አሁን፡ በሰበት ሕግ መሰረት ከሰራን፡ እያንዳንዱን መሬት ማጠጣት እንችላለን፡ ውኃውን ከሐይቆች ወስዶ ማጠጣት። ይህ ግን በሰበት ህግ መሰረት መሰራት ይጠበቅብናል። ቆመን በመመኘት አንሰራውም። ጮኸን በመናገር አይሆንም። በጫጫታችን አይሆንም። እዚያ ለመድረስ፡ በሰበት ህግ መሰረት መሰራት አለብን። እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በሕግ አስቀምጧልና።

124 እዚህ ጋር፡ አንድ ነገር አሰቤ ነበር፡ አስቀድሜ ነግሬአችሁ እንደሆነ፡ ወይም እንዳልሆነ አላውቅም። ከአንድ ዓመት በፊት፡ እኔና ወንድም ዉድ፡ ሽኮኮ ለማደን፡ ኬንታኪ ውስጥ ነበርን። እና... ሽኮኮዎቹ እምብዛም አልነበሩም፡ ስለዚህ ወደ አንድ ሰው ቤት፡ ስለ አደን ለማወቅ ሄድን። ብዙ ሄክታር መሬት የነበረው ሰው ሲሆን፡ መሬቱ በጫካ የተሞላ ነው። ወንድም ዉድ ስለ ሰውዬው፡ "ይህ ሰው ወግ አጥባቂ ነው። የ—የማያምን ነው፡" አለኝ። ስለዚህ እርሱን አውቀዋለሁ አለ፡ ስለዚህ እሱ... ወይም አባቱ ያውቁታል፡ እናም ሄዶ አደን እንድንሄድ ይፈቅድልን እንደሆነ ይጠይቀዋል።

125 ወደዚህ ጨዋ ሰው ቤት በመኪና ሄድን። እርሱም ከሌላ ሰው ጋር በፖም ዛፍ ሥር፡ ተቀምጦ ነበር፡ ሁለቱም በሰባዎቹ ዕድሜ ክልል ነበሩ። እናም ሚስተር ዉድ ወደዚህ ሰው ሄዶ፡ "መሬትህን ለአደን እንድሄድ ትፈቅዳለህን፡" በማለት ጠየቀው? እርሱም፡ "ይሁን፡" አለው፡ "እሺ" አለው። አክሎም እንዲህ አለው፡ "የየትኛው ውድ ልጅ ነህ? የጂም ዉድ ልጅ ነህን? "

እርሱም "አዎን ነኝ፡" አለው።

126 እንዲህም አለ፡ "ይሁን፡ ሽማግሌው ጂም ታማኝ ሰው ነበር፡ ወዘተ።" አክሎም፡ "በፈለክበት ቦታ፡ በእኔ ቦታ ማደን ትችላለህ። እዚህ **እጅግ-ብዙ** መቶ ሄክታር መሬት አለኝ፡ ዘና በል። እንደፈለጋችሁ፡ በተመቻችሁ ቦታዎች ሁሉ ውረዱ። ቤታችሁ እንደሆነ ቁጠሩት።"

127 እኔ ግን ሰባኪው እና ወግ አጥባቂ አብረው አይሄዱም ብዬ ሰላሰብኩ፡ መኪና ውስጥ ቁጭ ብዬ ነበር፡ ማለት ከወግ አጥባቂ እርዳታ መጠየቃችን

ከሆነ ብዬ ነው።

128 ስለዚህ ትንሽ ቆይቶ፡ ወንድም ዉድ እንዲህ አለ፡ "እሺ፡ እንግዲያውስ፡ ከእኔ ጋር ፓስተሬ መውሰድ እችላለሁን? አብሮኝ ቢመጣ ምንም አይደለም ብዬ እገምታለሁ።"

129 እና ሽማግሌው ዱላቸውን እንደያዙ ዞር በማለት፡ እንዲህ አሉ፡ "ዉድ፡ በሄድክበት ሁሉ ሰባኪ ይዘህ እስክትዞር ድረስ፡ ይሄን ያህል ራስህን እጅግ አዋርደሃልን? "

130 እና ስለዚህ፡ ከዚያ በኋላ፡ ከመኪናው ብወርድ ይሻለኛል፡ ብዬ አሰብኩ። እናም ከመኪናው ወርጄ፡ ከሽማግሌው ጋር ለጥቂት ደቂቃዎች ተነጋገርኩ። እና ስለሰባኪዎች ብዙም ክብር እንደሌለው ወዲያው አሳወቀኝ፡ ምክንያቱም ምንም በማያውቁት ነገር ይናገራሉ ብሎ ሰላሰበ ነው።

131 እንዲህም አለ፡ "እነሱ ምንም በማያውቁት ነገር እንዲሁ ይጮሃሉ። እንግዲህ፡" አክሎም "አንድ ሰው ሲያናግረኝ፡ የሚናገረውን የሚያውቅ እንዲሆን እፈልጋለሁ፡" አለኝ። እንግዲህ፡ ጥሩ ነገር ነው። ያ ጥሩ ነገር ነው። እንዲህ አለኝ፡ "እንግዲህ፡ አንድ ሰው ሲያናግረኝ፡ **የማይረባ-ነገር** እንዲናገር አልፈልግም፡ ምንም በማያውቀው ነገር እንዲገምት አልፈልግም። የሚለውን ነገር የሚያውቅ ሰው እንዲናገረኝ እፈልጋለሁ።" እንግዲህ፡ እኔም አከበርኩለት። ያንን ነገር ሽማግሌውን አከበርኩለት።

132 እኔም "ይሁን፡ በእርግጥ፡ ሁሉም ሰው ሃሳቡን የመግለጽ መብት አለው፡" አልኩት።

133 እርሱም፡ "ከጥቂት ዓመታት በፊት፡ ወደዚህ አገር መጥቶ አክተን ላይ፡ ጉባኤ ያደረገ አንድ ሰባኪ ነበረ።" እና እንዲህ አለ፡ "ይህ ሰባኪ፡ ለአገሩ እንግዳ ቢሆንም፡ አንድ ቀን ማታ ላይ፡ በጉባኤው ተቀምጣ ለነበረች አ—አንዲት እመቤት ተናገራት፡ 'ኪስሽ ውስጥ መሃረብ ይዘሻል። ሰምሽም ወይዘሮ **እከሌ-እና-እከሊት** ይባላል። እና እዚህ ኮረብታው ላይ የታመመች እህት አለሽ። ስሟ **እከሌ-እና-እከሊት** ትባላለች። በሆድ ካንሰር ተይዛ፡ እየሞተች ነው።' እንዲህም አላት፡ 'ይህን መሀረብ ወስደሽ እህትሽ ላይ አኑሪው፡ እንዲህም በያት፡ "**የሰራዊት ጌታ እግዚ አብሄር እንዲህ ይላል**፡ አትሞቺም፡ በህይወት ትኖሪአለሽ።"'"

134 እንዲህም አለ፡ "ይህች ሴት ጓደኛችን ነበረች።" እናም እንዲህ አለ፡ "ለሴቲቱም ይህን መሀረብ ይዘንላት ሄድን፡ ወይም፡ ሰውዬው፡ እ፡ ያ ሰው... " በመጀመሪያ እንዲህ አለ፡ "ይህቺ ሴት፡ እኔና ባለቤቴ በዚያን ቀን ጠዋት ወደሷ ሄድን፡ አብረናት ቆየን። ክፉኛ ተጎድታ ነበር! ዶክተሮቹ ተሰፋ ከቆረጡባት፡ እጅግ ቆይቷል። በአንሶላ እሰክናመላልሳት ድረስ ክፉኛ ተጎድታ ነበር፡ ወደ ላይ አንስተን በአልጋው ላይ ሰናስቀምጣት፡ መልሰን ሰናወርዳት ነበር። በአንሶላው ላይ ሰንገለብጣት፡ እጅግ ተጎድታለች።" እንዲህም አለ፡ "አንድ ቀን ምሽት፡ እዛ አካባቢ፡ አንድ ሰው የሞተ ሰው የመሰለ ድምጽ መጣ።"

135 ያም በዚያ የነበረው ቤን ይመስለኛል፡ ይያንን መሀረብ ይዞ፡ ወደዚያ ወሰደላት። አንተ ትመሰለኛለህ፡ አይደል፡ ቤን? [ወንድም ቤን ብራያንት "ኣሜን። ኣሜን፡" አለ።—አርታዒ።] ያኔ ወንድም ቤን ነበር፡ ያንን መሀረብ ይዞ፡ ወደ ሴቲቱ አመጣ።

136 እንዲህም አለ፡ “በማግስቱ ጠዋት፡ የተጠበሰ የአፕል ኬክ መብላት ጀመረች።” አክሎም አለ፡ “የራሷ ስራ ብቻ ሳይሆን፡ የጎሮቤት ስራም መስራት ጀመረች። እጅግ ጤነኛ ሆነች!” እንዲህም አለ፡ “አሁን እንዳንዴ እሰበዋለሁ። ያ ሰባኪ የማየት ዕድል ባገኝ፡ እርሱ የሚናገረውን የሚያውቅ ሰባኪ ነውና፡” “ባነጋግረው ደስ ይ—ይለኛል፡” አለ።

137 ወንድም ዉድ አየት አደረገኝ፡ እኔም እሱን አየሁት። ጫካው ውስጥ ከመሰፈራችን የተነሣ፡ በላብና እድፈት፡ ቆሽሸን፡ እ—እና በሸኮኮ ደም ተሸፍነን፡ ቆመን ነበር። እኔም፡ “እሺ፡” አልኩት፡ “እና... ከዚህ ሰው ጋር ብትነጋገር እንዴት እንደሆነ ይነግርሃል ማለትህ ነውን” አልኩት?

እርሱም፡ “አዎን፡ ወዳጄ፡ እንደዚያ ማለቴ ነው” አለኝ።

እኔም፡ “እሺ፡ በ—በጣም ጥሩ ነው” አልኩት።

138 ከፖሞቹ አንዱን እየበላሁ ነበር። ዓመቱ ደረቅ ወቅት፡ ነሐሴ ላይ ነበርና፡ ታውቃላችሁ፡ ትናንሽ ትሎች በላያቸው ላይ ነበሩበት። ስለዚህ ትንሽ ፖም ይዤ፡ እየበላሁ ነበር። ያን ጊዜ እንዲህ አልኩት፡ “በጣም ጥሩ ፖም ነው።” “ዛፉ ምን ያህል ጊዜ ሆነው፡” አልኩት?

139 “ኦህ፡” “ያንን ዛፍ እዚያ ከተከልኩት ሠላሳ፡ ወይም፡ አርባ ዓመታት ሆኖኛል፡” አለኝ።

140 “አዎን፡ ወዳጄ።” “አንድ ጥያቄ ብቻ ልጠይቅህ እፈልጋለሁ፡” አልኩት። አልኩትም፡ “ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል... እነዚህ ፖሞች ከዚህ ዛፍ ላይ ሲወድቁ እያየሁ ነው፡ ቅጠሎቹም እየረገፉ ነው፡ ነገር ግን የነሀሴ አጋማሽ ነው።” አልኩትም፡ “ቀዝቃዛ ወራት ገና አልመጡም፡ በረዶም እየወረደ አይደለም፡ ይሁን እንጂ ቅጠሎቹ ከዛፉ እየረገፉ ናቸው። ይህ ለምን ሆነ? ”

እርሱም “የዛፉ ሰም ከዛፉ ስለወጣ፡” አለኝ።

እኔም፡ “ኦህ” አልኩት፡ “ወዴት ሄደ? ”

እሱም፡ “ወደ ሥሩ ወረደ” አለኝ።

እኔም፡ “ታዲያ እስከ መቼ እዚያ ይቆያል” አልኩት?

“እስከ ፀደይ ድረስ፡” አለኝ።

141 እኔም፡ “ስለዚህ ያን ጊዜ እንደገና ይወጣል፡ የምታጠልበት አዲስ ቅጠሎችን፡ የምትበላውን አዲስ ፖም ያወጣል።”

“ትክክል። በትክክል፡” አለኝ።

142 እኔም፡ “እንግዲያውስ፡ ወዳጄ ሆይ፡ አንዲት ጥያቄ ልጠይቅህ። ስለ እነዚህ ሰዎች ስለ ምን እንደሚናገሩ ስለማያውቁ ሰዎች ተናግረሃልና።” እንዲህ ብዬ ጠየቅኩት፡ “ያንን የዛፉ ሰም ከዛፉ እንዲወጣ ያደረገው አካል ማን እንደሆነ ልትነግረኝ ትችላለህን? በክረምቱ ወቅት እዚያ ከቆየ፡ ዛፉ ይሞታል። ዛፉን ትገድለዋለህ። የሕይወት ጀርም በዚያ የዛፍ ሰም ውስጥ ይገኛልና።” ስለዚህ አልኩት፡ “ዛፉን ሊገድለው ይችላል። እና ጸደይ እስኪመለስ ድረስ፡ ያንን የዛፉ ሰም፡ ወደ ታች ወደ ስሩ እንዲወርድ ያሰደረገው አካል ማን ነው፡ ከዚያም እንደገና ተመልሶ የፖም ፍሬ እንዲሰጥ ማን ያዘዋል? ” እኔም፡ “አንድ ባልዲ ውሃ ሙላና ግንድ ላይ አስቀምጠው፡ እናም ተመልከት፡ በነሐሴ ወር

ወደ ምሰሶው ሥር ወርዶ በፀደይ ወቅት እንደሚነሳ፡ ተመልከት። አየህ?”
አልኩትም፡ “የሆነ ሕግ አለ፡ የተፈጥሮ ሕግ አለ። ይህ ሕግ በቅደም ተከተል ያስቀመጠ የሆነ አካል አለ። ይህ ብቻ ሳይሆን፡ ያው አካል ራሱ ይህን ህግ እንዲሰራ ያከናውነዋል፡ ወደ ዛፉ ስር ያወርደዋል፡ እንደገናም ይመልሣል።”

እሱም “ስለዚህ አስቤው አላውቅም፡” አለ።

143 እኔም እንዲህ አልኩት፡ “ይህን ከቻልክ… ያንን ሰም የዛፉን ቅርንጫፎች ትቶ ወደ ዛፉ ሰሮች እንዲወርድ ያስቻለው አካል፡ ተመልሶም እንዲመጣም ያደረገው ያ አካል፡ ያን ቀን ማታ ላይ በዚያ ቦታ እንዲህ በማለት የተናገረኝ እርሱ ነው፡ ‘ሂዱና፡ በሴቲቱ ላይ መሀረቡን አድርጉባት።’”

እንዲህም አለ፡ “ስለዚህ ያ ሰባኪ አንተ ነህን?”

“አዎን፡ ወዳጄ፡ ትክክል ነው፡” አልኩት።

144 ባለፈው ዓመት በዚያ ነበርኩና (ሞቷል)፡ መበለቲቱም በረንዳ ላይ ተቀምጣ፡ ከዚያ ዛፍ ላይ፡ ፖም እየላጠች ነበር። ወንድሜ… መጀመሪያ እኛን ሊያሰወጡን ሞክረው ነበር፡ እነማን እንደሆንን አላወቁም ነበር። እኔም ወደሷ ሄጄ፡ ከእርሱ ፈቃድ እንዳለን ነገርኳት። ስለ ጉዳዩም ነገረችኝ፡ እንዲህም አለች፡ “ከመሞቱ በፊት ክርስቶስን ሙሉ በሙሉ ተቀብሏል።”

145 እያችሁ፡ ያንን ዛፍ ማን ነገረው፡ ወደ ታች እንዲወርድ የመራው አካል ማን ነው? ሕግ ነው። እግዚአብሔር በሰርዓት ቅደም ተከተል ያስቀመጠው ሕግ። እና ያ ህግ ጉዳዩን የሚቆጣጠር የእግዚአብሔር ህግ ነው። ኣሜን።

146 ይኸውላችሁ፡ ምን ያህል ብታለቃቅሱ፡ እንዲህ—እና እንዲያ ብትሉ አይገደኝም፡ “እንዲህ የሚሆን አይመስለኝም፡ በዚህ የበጋ ወቅት ጸሐይ ከእንግዲህ የምትበራ አይመስለኝም።” መብራቷ፡ የማይቀር ነው። እንዲሁም፡ “እ—እ—እንዲመሸ አልፈልገውም” ብትሉ አይገደኝም። እንዲሁ፡ መምጣቱ የማይቀር ነው። ምክንያቱም ይህ የምንኖርበት፡ ዓለም ተብሎ የሚጠራው ነገር፡ በእግዚአብሔር ሕግ ቁጥጥር ሰር ነው።

147 አሁን፡ ወንድሞች እና እህቶች ሆይ፡ አንድ ነገር ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ። ስለዚህ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ዳግመኛ ከተወለድን… እግዚአብሔር ትንሽ ደካማ ክፍሎች እና ትላልቅ ጠንካራ ክፍሎች የሉትም፡ እሱ በአጠቃላይ አምላክ ነው! ስለዚህ በውስጣችሁ በቂ የሆነ አምላክ ካለ፡ ያም ምንም ያህል ጥላ ቢያክልም እንኳ፡ አንዲስ ምድር የመፍጠር በቂ ኃይል አለው። አዲስ ጨረቃ እና አዲስ ሰርዓት ለመፍጠር በቂ ኃይል አለው። እግዚአብሔር ነው፡ ጉልበታም ነው! አሁንም እዚህ ያለው አማኝ ሁሉ የዘላለም ሕይወት አለው፡ ያም፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ውስጥ በመሆኑ ነው፥ ሙታንን ለማስነሳት፣ የታመሙትን ለመፈወስ፣ ምህዋሮችን ለመመለስ የሚያስችል በቂ ሃይል ነው። እናንተ ግን፡ ይህ በእናንተ ያለው መንፈስ፡ የሚመራው በሕግ ነው። እናንተም የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ናችሁ። በእናንተ ያለው ይህ መንፈስ፡ በትንሣኤ ቀን የሚያስነሳችሁ እርሱ ነው።

148 ኢየሱስ፡ በዚህ ምድር ሳለ፡ ሲሞት፡ ነፍሱ ወደ ሲኦል ወረደች፡ “በእስር ላሉት መናፍስት ሰበከ፡ በእስር ላሉት ነፍሳት፣ በኖኅ ዘመን በታገሳቸው ጊዜ ንስሐ ላልገቡ ነፍሳት ሰበከላቸው።” ሰውነቱ ወደ መቃብር ገባ። ከመሞቱ

በፊት ግን፡ መንፈሱን በእግዚአብሔር እጅ አኖረ። መንፈሱ ወደ እግዚአብሔር ሄደ፡ ነፍሱ ወደ ሲኦል ሄደ፡ ሥጋውም ወደ መቃብር ሄደ። ቅዱሳት መጻሕፍት እስኪፈጸሙ ድረስ ኢየሱስ አልተነሣም። ተመልሶ መምጣት አልቻለም፡ ምክንያቱም በመቃብር ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት መቆየት ነበረበት። ቅዱሳት መጻሕፍት ሙሉ በሙሉ ሲፈጸሙ ግን፡ ይህ እንቅፋት ተወገደለት፥ መንፈሱ ወደ ነፍሱ፣ ነፍሱ ወደ ሥጋው ወረደች፣ እናም ተነሣ።

149 ስንሞትም፡ ነፍሳችን በእግዚአብሔር መሠዊያ ሥር ትገባለች፥ እኔ ራሴ በራእይ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚናገርለት ነገር፡ እንደምታውቁት፡ ከጥቂት ማለዳዎች በፊት፡ የማየት ዕድል አግኝቻለሁ፡ “መንፈሳችን ወደሚሰጠን አምላክ ይሄዳል፡ ሰውነታችንም ወደ ምድር አፈር ይመለሳል።” አንድ ቀን፡ መጽሐፍ ሲፈጸም ግን፡ መንፈሳችን ከእግዚአብሔር ይለቀቃል፡ ነፍስን ያነሣታል፡ እና ነፍስን ወደ ሥጋ ይመልሳታል። የሚያስነሳንም ኃይል አሁን፡ በእኛ ውስጥ አለ! አሁን ያለነው በሰማያዊ ሰፍራ ነው። አሁን በትንሣኤ ኃይል ውስጥ ነን።

150 ለዚያ ህግ ባይኖር ኖሮ፡ የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ዓለምን ፈጥረው በዚያ ላይ የግል ሕይወት ለመኖር ይወጡ ነበር። ይህን ማድረግ የምትችሉበት ኃይል በውስጣችሁ አለ። በውስጣችሁ የእግዚአብሄር የኃይሉ ጥላ ካለ፡ ይህን የምታደርጉበት ኃይል አላችሁ። እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው። ምን ለማለት እንደፈለግኩ ተመልከቱ? በእናንተ ውስጥ ያለው ኃይል ይሠራል፡ ዓለምን ወደ መኖር ተናግራችሁ በእሱ ላይ መኖር ትችላላችሁ። ሃሌ ሉያ! ይኸው።

151 አሁን በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለው ኃይል ይህ ነው፡ ነገር ግን በህግ ቁጥጥር ስር ነው። ሕጉም “የትእዛዛት ብዛት መጠበቅ” አይደለም። የእምነት ሕግ ነው። ኢየሱስም፡ “ለሚያምኑ ሁሉ ይቻላቸዋል” ብሏል። እናም፡ ካመንክ፡ እግዚአብሔር ነፍስህን እንድታምን የሚመራው ነገር ሁሉ፡ የአንተ ነው። የእግራችሁ ጫማ የሚረግጣትን ቦታ ሁሉ፡ እግዚአብሔር፡ በእምነት ይሰጣችኋል። አሜን! የዚህ የእምነት ህግ ቁልፍ እስካገኘህ ድረስ፡ የአንተ ነው፡ ንብረትህ አድርገው። ምን ማለቴ እንደሆነ አያችሁ? ይህ ኃይል የሚቆጣጠረው በ... የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ፡ ወይም የእግዚአብሔር ሴት ልጅ ከሆንሽ፡ ይህ ኃይል ፈጽሞ አይተውህም። ሁል ጊዜ ከአንተ ጋር ነው። ነገር ግን፡ እምነትህ ከእርሱ እየራቀ ቢሆንም፡ ነገር ግን አሁንም አለ። ሃሌሉያ!

152 ሰትድን፡ እግዚአብሔር ከምድር ጭቃ እንድትነሳ እምነት ይሰጥሃል። እምነትህ የዓለምን ነገር ያሸንፋል። እምነትህ ምንድን ነው? የእግዚአብሔር ልጅ እንድትሆን፡ እግዚአብሔር ባንተ ባደረገው ተግባር ላይ ያለህ እምነት ነው። ውሸትን ትተሃል፣ መሰረቅህን ትተሃል፣ መጠጥህን ትተሃል፣ ምክንያቱም እምነትህ ከሱ በላይ ስለሚያደርግህ ነው። አሜን። ይህን ማድረግ ካልቻልክ፡ ምንም እምነት የለህም። “በእምነት ድናችኋል፡ ይህም በጸጋ ነው።”

153 እምነታችሁን የሚዘረጋውን ያህል፡ ኃይላችሁም ያን ያህል ይሆናል፡ ምክንያቱም በውስጣችሁ ሰማይንና ምድርን የመሥራት ኃይል አለና። እግዚአብሔር በእናንተ ያድራል፣ እናንተም የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ናችሁ። አሜን! ይኸው ነው። ግን፡ እምነትህ ነው። ኢየሱስም ሲናገር፡

“እንደ እምነትህ፡ ይሁንልህ። ለሚያምን፡ ሁሉ ይቻላል። እውነት እላችኋለሁ፡ ይህን ተራራ፡ ‘ተንቀሳቀስ፡’ ብትሉት፡ ባትጠራጠሩም፡ ነገር ግን የተናገራችሁትን ነገር ብታምኑት!”

154 እንግዲህ በእኛ በሚኖረው በዚህ በታላቅ ቤዛ በክርስቶስ አምነን፡ እርሱ ከቤተ ክርስቲያን የማይወጣ የተመታው አለት ነውና፡ ምን ዓይነት ሰዎች መሆን በተገባን ነበር? “እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ፡” ከቀራንዮ ወደ ቤተክርስቲያን የፈሰሰው ታላቁ የድኅነት እና የኃይል ምንጭ ፍጹም-የማያቋርጥ፡ ከሕያው እግዚአብሔር ዘንድ ፍጹም-የማያቋርጥ፡ ታላቅ ምንጭ፡ በጉዞአችን ከእኛ ጋር የሚራመድ የተመታው አለት ነው።

155 እስራኤል እምነቷን ጣለች። ከመንገድ ወጡ። የስጋ ምንቸቶች መመኘት ጀመሩ። እግዚአብሔር ወደ ምድሪቱ እንደሚያደርሳቸው አምነው፡ በእምነታቸው ቢጸኑ፡ የሚያደናቅፋቸው ነገር ባልነበረ ነበር። ቀድሞውንም ባሕሮችን ከፍለው ነበርና፡ በጠላቶቻቸው ላይ መቅሠፍት አወረዱ፡ ጠላቶቻቸውን ከኋላቸው ሰቅለው፡ ወደ ምድሪቱ ተጉዘው ነበር፡ ቢሆንም ወደ ተስፋው ለመሄድ እምነት ሊኖራቸው አልቻለም።

156 ኢያሱና ካሌብ እምነት ነበራቸው! እንዲህም አሉ፡ “ከፊታችን የሚመጣውን ማንኛውንም ነገር ማሸነፍ ከመቻል በላይ ነን።”

157 የቤተ ክርስቲያን ችግር ይህ ነው። ማንኛውንም በሽታ ማሸነፍ እንችላለን። ኃይሉ በውስጣችን አለ። እኛ የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ነን፡ ምንም ነገር በፊታችን ሊቆም አይችልም። ብቸኛው ነገር፡ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያደረገላችሁን፡ የሚያምን ሰው ማግኘት ይፈልጋል። ወደፊት እንዲህ **እንሆናለን** አይደለም፥ አሁን ነን! ፍጹም-የማያቋርጥ መንፈስም ከእኛ ጋር ነው። አሜን! ይኸው ነው።

158 ዛሬ ጠዋት ስለ ርዕሰ ጉዳዩ፡ **ፍጹም-የማያቋርጥ ከአለቱ የወጣ ውኃ** ብዬ ሰናገር ስለዚህ ነው። ፍጹም-የማያቋርጥ ከአለቱ የወጣ ውኃ አሁን እዚህ አለ፡ ያ በቀራንዮ የተመታው ፍጹም-የማያቋርጥ ውኃ አለ። ያ መንፈስ ቅዱስ በቀራንዮ ከእርሱ በወጣ ጊዜ፣ በጴንጤቆስጤ ቀን በቤተክርስቲያን ተመልሶ የመጣው፣ ዛሬ ጠዋት ያ መንፈስ ቅዱስ አለ። እና ቃል ኪዳን ይሰጠናል!

159 እርሱ ያኔ አገልግሎት በሰጠኝ ጊዜ፡ በታመሙ ሰዎች ፊት መሄዴ፡ ምክንያቱ ይህ ነው፡ እኔም አመንኩት፡ እግዚአብሔር ተናግሯልና! ራእዮች የሚከሰቱት እንደዚህ ነው፥ እግዚአብሔር ቃል ገባ! እግዚአብሔር ሊዋሽ አይችልም።

160 እመኑት! ማመን አለባችሁ። ያንን መዝጊያ መክፈት የሚያስችል ነገር፡ እናንተ ትገቡ ዘንድ የሚያስችል፡ አንዳች ነገር ሊኖር ይገባል። ዛሬ የምንፈልገው ለበለጠ ኃይል መጸለይ አይደለም። አዲስ ምድር ለመፍጠር የሚያስችል በቂ ኃይል አላችሁ። ይህን ሃይል ለመጠቀም እምነት የሚያስፈልገው ነገር ነው። የሚያስፈልጋችሁ ነገር ያንን ህይወት መቆጣጠር መቻል ነው፡ ከዚያም እግዚአብሔርን የመምሰል ህይወት ኑሩ፡ ያን ጊዜ ከእግዚአብሔር የምትለምኑት ነገር ሁሉ፡ ታውቃላችሁ! በዚህም፡ በእግዚአብሔር ድፍረት አለን። ትእዛዛቱን ከጠበቅን፡ ከእርሱ ጋር ብንመላለስ፡ መልካም ነገርን እንደማይነፍገን፡ እናውቃለን። ከእኛ ጋር የሚሄድ አምላክ ነው። ኦህ፡ ማይ!

161 አንድ ነገር ብቻ ማድረግ ነበራቸው። አንድ ነገር ብቻ ማድረግ ነበራቸው፡ ያም፡ ከመንገድ አለመውጣት ነው። **ወደዚህ** አለመቅበዝበዝ፡ **ወደዚያም** አለመቅበዝበዝ፥ መንገዱ ላይ መጽናት! ቤተክርስቲያን አንድ ነገር ብቻ ማድረግ አለባት፡ ከመንገዱ አለመውጣት! ሲከተሉትም፡ የእሳት ዓምዱ በመንገዱ ላይ ይጠብቃቸው ዘንድ፡ ከነሱ ጋር የነበረ የእሳት ዓምድ ነበራቸው። የመራቸውም ይሄው ነው። ያዩት ነገር፡ ይህ የእሳት ዓምድ ነው። በሙሴ በኩል ሲሰራ አይተውታል፣ እና እሱ መሪ እንደሆነ ያውቃሉ።

162 ዛሬ ቃሉ አለን። ቃሉን እንከተላለን። ቃሉም በአማኞች ውስጥ ሲሰራ እናያለን፡ እናም፡ ትክክለኛ ነገር እንደሆነ እናውቃለን። በሚከተሉት ምልክቶች ቃሉን ያጸና እግዚአብሔር፡ ከእኛ ጋር ይሰራል! ከቃሉ ጋር እንቆያለን። ቃሉ ውጤቱን ያመጣል።

163 ከሙሴ ጋር ጸኑ። ምክንያቱም፡ ሙሴ፡ ያንን የእሳት ዓምድ ተከትሏል። እነሱም ተከተሉት። በሙሴ ላይ መቃወምና፡ በእግዚአብሔርና በሙሴ ላይ መነሣሣት በጀመሩ ጊዜ፡ ወዲህ እና ወዲያ ተቅበዘበዙ። ችግሮች ገቡ። በትክክል።

164 ከቃሉ ጋር እንቆያለን፡ ቃሉም ምልክቶችን ያደርጋል። ኢየሱስም “ቃሉን ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፡” ብሏል። አያችሁ፡ መጽናት ብቻ ነው… ከቃሉ ጋር ከጸናችሁ፡ ቃሉ ምልክቶችን ያደርጋል። ሙሴ፡ ግን፡ ምን አደረገ?

165 ተቅበዘበዙ፡ ምን አደረጉ? ከመንገድ ወጥተው ተቅበዘበዙ፡ የውኃ ምንጫቸውን አጡ።

166 ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ያደረገችው ይህንኑ ይመስለኛል። ከቅዱሳት መጻሕፍት መንገድ ወጥተው ተቅበዝብዟል። በርእዮተ ዓለሞች ተወሰደዋል። መሄድ ወደሌለባቸው ጥቃቅን ነገሮች ሄደዋል። ነገሮች ተቀብለዋል። እንደ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ያሉ ነገሮችን ተቀብለዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህን ከየት አገኘኸው? የሚያነቡትን ካቴኪዝም ተቀበሉ። ከልምምድ ይልቅ የሐይማኖት ተቋማትን ተቀብለዋል። ከዳግም-ልደት ልምምድ ይልቅ መጨባበጥን ተቀበሉ። ከውኃ ጥምቀት ይልቅ መርጨትን ተቀበሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደዚህ ያለ ነገር ባይኖርም፡ “አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ፡” በማለት ክፉ ነገር ተቀበሉ። መጽሀፍ ቅዱስ ግን፡ “በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ያዛል!” ያንኑ ውኃ ወደዚያ መንገድ እንዲመጣላችሁ ከፈለጋችሁ፡ ማድረግ ያለባችሁ አንድ ነገር ብቻ አለ። ወደ’ሱ ተመለሱ… እርሱ አልተዋችሁም፥ አሁንም ህያው ነው። በክርስቶስ ፈንታ የሐይማኖት መግለጫ ተቀበላችሁ። በማጉረምረም ተቅበዘበዛችሁ።

167 አንዱ “እኔ፡ ሜቶዲስት ነኝ፡” ይላል።

ሌላኛውም “እኔ ባፕቲስት ነኝ፡” ይላል።

ይህ የሚያሳየው፡ ክርስቲያን እንዳልሆንክ ነው። እኛ የክርስቶስ ነን! እኛ የሱ ነን።

እንዲህ ትላለህን፡ “እንግዲህ፡ እኔ፡ ባፕቲስት፡ አይደለሁም? ”

ያ ብቻ ከሆንክ፡ አንተ የክርስቶስ አይደለህም፡ ባፕቲስት ነህ።

"እንግዲህ፡ እኔ ጴንጤ ነኝ፡" ትላላችሁ።

በሐይማኖት ተቋም ደረጃ ጴንጤ ናችሁ፡ ይኸው ናችሁ።

168 ይሁን እንጂ፡ የጴንጤቆስጤ ልምምድ ካላችሁ! የጴንጤቆስጤው ቃል ደግሞ የጴንጤቆስጤ ልምምድን ያመጣል! እነዚያ ደቀ መዛሙርት ያደረጉትን ተመሳሳይ ነገር ተከተል፣ በመንፈስ ቅዱስ እስክትሞላ ድረስ በዚያ ቆይ።

169 እና ከዚያ በኋላ በአጋጣሚ ከቃሉ ጋር የሚቃረን ድርጊት ከፈጸማችሁ፡ ያ በእናንተ ውስጥ ያለው መንፈስ ቃሉ የሚለውን የሚቃወም ከሆነ፣ መንፈስ ቅዱስ አይደለም። መንፈስ ቅዱስን የሚመስለው ዲያብሎስ ነው። የት እንዳለን ታያላችሁን? ኦህ፣ አንዳንዶቻችን በልሳን ተናግረናል፣ የጩህት ክፍሎች እና መሰል ነገሮች አሉብን፣ እና እነዚህን ሁሉ ሌሎች ነገሮች እንክዳለን። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ያልነበረውን ሁሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን አስገብተናል በዚህ ሁሉ ዝም ብለናል። ዛሬ የት ነን? ራሳችንን እንደገና በሌላ በረሃ፡ በደረቀ ድርጅት ውስጥ እናገኛለን። እራሳችንን አደራጅተን፡ ውሃ አጥተናል። ጴንጤዎች ያደረጉትም ይህንኑ ነው። መደራጀት ሲጀምሩ፡ ህብረቱን ማፍረስ ጀመሩ፡ እንዲህም አሉ፡ "አሁን፡ ይሄ ሰውዬ **እንዲህ** የሚያምን ከሆነ፡ አብረን አንሰራም።"

170 ወደ እውነት ቃል፡ እውነትን ወደ ማወቅ እስኪመጣ ድረስ፡ ሂድ ከእርሱም ጋር ተቀመጥ። ምንም ይሁን ምን፡ ለማንኛውም፡ ዝም በል። ልክ እንደ ወንድማማቾች ሁኑ፡ ወደ ፊት ቀጥሉ።

171 ነገር ግን፣ ኦህ፣ እራሳችንን አደራጀን፡ እንዲህ አልን፡ "እሺ፡ አንድ አምላክ አማኞች ስላልሆናችሁ፣ ሁለት አምላክ አማልክ አምኞች ስላልሆናችሁ፡ ወይም ስላሴ፡ ወይም **እንደዚህ** አይነት ነገሮች ስላልሆናችሁ፡ ከእናንተ ጋር ህብረት አይኖረንም።" ታዲያ ይህን ስናደርግ፡ ምን እየሰራን ነው? እንደገና በረሃ ውስጥ ራሳችንን እናገኛለን። እውነት ነው!

172 ነገር ግን፡ አስታውሱ፡ እስራኤል ወደ ተስፋይቱ ምድር ከሚወስደው ወጥተው፡ ከመንገድ ወጥተው በተቅበዘበዙ ጊዜ፡ ዓለቱ ፈጽሞ አልተዋቸውም፤ እዚያም ነበረ፡ ውሃውም እንዲሁ ሆነ። መንፈስ ቅዱስም ተመሳሳይ ነው፡ እሱም እዚያ ይቆያል። ወደ ኋላ መቅበዝበዝ የለብንም።

173 አሁን፡ እዚህ ጋር እግዚአብሔር ታላቅ ነገር ያስተምረናል። እግዚአብሔር እዚህ ትምህርት እያስተማረን ነው። የጴንጤቆስጤን ልምምድ፡ ለአንዴና፡ ለመጨረሻ ጊዜ ሊሰጠን፡ ክርስቶስ አንድ ጊዜ ተመታ። ስለዚህ፡ አለቱ በተመታ ጊዜ፡ እንደገና መምታት አያስፈልግም ነበር። አስቀድሞ አንድ ጊዜ ተመትቶ ነበር።

174 ሙሴ ማስተሰርያው ላይ የነበረውን እምነት ደካማነት በማሳየት፡ ለሁለተኛ ጊዜ በመምታቱ ስህተት ሰርቷል። ነገር ግን ክርስቶስ አንድ ጊዜ በተመታ ጊዜ፡ እንደገና መመታት እንዳልነበረበት እናውቃለን። እሺ፡ ሙሴ ምን እያደረገ ነበር? ሙሴ አዲስ ነገር በማዘጋጀት ላይ ነበረ፡ አንዲስ ነገር ለማድረግ ሞከረ።

175 እና የእኛ ቀሳውስት ዛሬ ያደረጉት በዚህ መንገድ ነው። አዲስ ነገር ለመስራት ሞከሩ። "ራሳችንን አሴምቢሊስ ኦፍ ጋድ እናደርጋለን። ራሳችንን ጴንጤቆስጣል ቸርች ኦፍ ጋድ እናደርጋለን። እራሳችንን ጠቅላይ ምክር

ቤት እናደርጋለን። እራሳችንን **ይህንን፡ ያንን፡** ወይም **ሌላ** እናደርጋለን።” እግዚአብሔር ያደረገው ያ አይደለም። ያ የእሱ ሀሳብ አልነበረም።

176 ክርስቶስ አንድ ጊዜ ተመታ። ያ የመጀመሪያው ልምምድ ነው። ዋናው መንገድ ያ ነው። በጴንጤቆስጤ ዕለት፡ ጴጥሮስ እንዲህ አለ፡ “ንስሐ ግቡ፡ እያንዳንዳችሁም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ።”

177 “እኛ ‘በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ’ ስም እንረጫለን፡ ህጻናቶቹን የሐይማኖት መግለጫ እና ሌላው ነገር ሁሉ እንሰጣቸኋለን።” ከቃሉ ሰንወጣ፡ የትም መድረስ አለመቻላችን አያስገርምም። አያችሁ?

178 እግዚአብሔር ትምህርት ይሰጠናል። ሙሴ እንዲህ ማለት አልነበረበትም፡ “አሁን እዚህ አዲስ ነገር እንጀምራለን፡ እናደራጃለን እና የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን እናደርጋለን።” ያደረጉት የመጀመሪያው ነገር ያ ነው። አይ፡ ከዚያ በኋላ እንዲህ እናደርጋለን፡ “እሺ፡ ከዚያ በመነሣት አዲስ ነገሮች እንሰራለን፡ ሉተራኖችን እናደርጋለን።” ከዚያም አንግሊካን መጡ፡ ከዚያም ባፕቲስት፡ እና ሌላ ምን አለ፡ እና ካምቤሊቶች፡ ቸርች ኦፍ ክራይስት፡ እና ጸረ ክርስቶስ፡ እና ሌሎች ነገሮች መጡ። አያችሁ፡ ሁሉም አንድ በአንድ፡ አንዱ በሌላው፡ የሐይማኖት ተቋማት እና ድርጅቶች እየፈጠሩ መሄድ ጀመሩ። መሆን አልነበረበትም። ያደረጉትን አያችሁ? አዲስ ነገር ለመጀመር፡ አለቱን እንደገና እየመቱት ነው። አዲስ ትምህርት አያስፈልገንም።

179 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቀ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንፈስ ቅዱስን ያገኘ ሰው ሁሉ፡ በእግዚአብሔር መንገድ መጥተዋል፡ በትክክል እግዚአብሔር ባደረገው መንገድ ተጉዘዋል። እነሱም ተመሳሳይ ነገር አደረጉ። ተመሳሳይ ልምምድ ነበራቸው። ተመሳሳይ ምልክቶች ተከተሏቸው። ተመሳሳይ ስራዎች ተከትሏቸዋል። ለምን? በአለቱ አጠገብ ኖረዋል። ተመሳሳይ ውሃ ጠጥተዋል።

180 እና፡ ዛሬም፡ እጅግ ብዙ የሐይማኖት መግለጫዎች እና የሐይማኖት ተቋማት የበዙብን፡ ምክንያቱም አዲስ ነገር በመጀመራችን ነው። ምንም አዲስ ነገር አያስፈልገንም። ዞር በል ከዚህ!

181 ሙሴ ዓለቱን እንደገና መምታት፡ አዲስ ነገር መጀመር አልነበረበትም። ከመጀመሪያው ዓለት፡ ሊያናግራቸው ይገባው ነበር። ኦህ፡ እንደምትረዱት ተስፋ አደርጋለሁ! ሙሴ ስለ መጀመሪያው፡ ስለተመታ አለት መናገር ነበረበት፥ እንደገና ለመምታት መሞከር ሳይሆን፡ አዲስ ነገር ለመጀመር መሞከር ሳይሆን፡ የጥንቱን ነገር ሊያናግረው ይገባ ነበር።

182 አምላክ ሆይ፡ እርዳኝ! ድሃ ሆኜ ብሞትም እንኳ፡ በመድረክ ላይ፡ ስለ ዋናው አለት እናገራለሁ! ስለ መጀመሪያው ልምምድ እናገራለሁ። የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ስለሰጣቸው የመጀመሪያዎቹ ቅዱሳት መጻሕፍት እናገራለሁ፣ “ንስሐ ግቡ፡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ፡ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።” ከዓለቱ የሚፈሱት ፍጹም-የማያቋርጡ ውኃዎች ከእኛ ጋር ናቸው። ተመሳሳይ ነገር ያመጣል። ራዕይን ያመጣል። ፈውሶችን ያመጣል። ትንቢቶችን ያመጣል። ያኔ ያደረጉትን ሁሉ ያመጣል።

183 እስራኤል እንደገና ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት በተመለሰች ጊዜ፡ መንገዱን አገኙት፡ ወደ ተሰፋይቱ ምድርም ተመለሱ። ነገር ግን አርባ ዓመት ወሰደባቸው።

184 ጰንጤቆስጤ አርባ ወይም ሃምሳ ዓመት ያህል ሆኖታል፣ በምድረ በዳ ይቅበዘበዛል። ወደ አለቱ ተመለሱ! ይታያልና። ይኸው እዚህ አለ፡ እዚህ በቃሉ ውስጥ ተጽፏልና። መንፈስ ቅዱስ ያኔም ያደረጋቸውን ነገሮች እየፈፀመ ነው፡ ስለዚህ ፍጹም-የማያቋርጥ ውኃ ህያው ነው። ብቻ ወደ እርሱ ተመለሱ፡ ወደ ፊተኛው፡ ወደ ዋናው ተመለሱ። ያኔ በዋናው የነበረው እንዴት ነበር?

185 "እሺ፡ ከሰባኪው ጋር እጅ ተጨባበጡን"? እንደዚህ ያለ ነገር አልነበረም። "'በአባት፡ በልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ' ተጠመቁን"? እንደዚህ ያለ ነገር አልነበረም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ወይም ከዚያ ውጪ፡ እስከ ሦስት መቶ ዓመታት ድረስ፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ በየትኛውም ቦታም መቼም ቢሆን አንድም በዚያ አልተጠመቀም፡ "በአባት፡ በልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ" የተጠመቀ አንድም ሰው የለም። ያ የካቶሊክ ሀይማኖት መግለጫ እንጂ፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አይደለም። አያችሁ?

186 መንፈስ ቅዱስ ነበራቸው። ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ተከተሉአቸው። ዛሬም እንደገና ያደርገዋል። ያ አለት ዛሬም እንደወትሮው ፍጹም-የማያቋርጥ፡ የተመታው አለት ነው!

187 "እንግዲህ፡ አሁን መጥተህ ወደ ጴንጤቆስጤ ቤተክርስቲያናችን ተቀላቀል፣ ወደ ጴንጤ ግዛታችን ግባ፡" እንበል። "አይደለም፡ እናንተ ወደ ባፕቲስት፡ ወይም ወደ ሜቶዲስት፡ ወይም ፕሬስባይቴሪያን፡ ወይም ወደ ካቶሊክ ኑ።" ያ ምንድን ነው? ያ አለቱን እንደገና መምታት፣ አዲስ ነገር ለመጀመር መሞከር ነው።

188 እንዲህ በላቸው፡ "ንስሓ ግቡ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም ተጠመቁ፡" ስለ ሐጢአቶች ስርየት፡ "ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል።" አሁን ወደ መንገዱ ተመለሱ፡ ወደዚያው ውኃው ተመለሱ። ያው ውኃ በተመሳሳይ መንገድ ያድሳችኋል። ለሰውነት ተመሳሳይ ተግሳጽ ይገርፋል። ተመሳሳይ የማጽዳት ኃይልን ይሰጣል። ተመሳሳይ የፈውስ ኃይል ይሰጣል። ወደዚያው መንፈስ ብቻ እንመለስ እንጂ፡ ያኔ ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር ያደርጋል።

189 በወይን ግንድ ውስጥ ያለ ሕይወት ወይን ያፈራል። ባለፈው አመት ካፈራ፡ በዚህ አመትም ተመሳሳይ ነገር ያፈራል። ያ የእግዚአብሔር ህግ ነው። የእግዚአብሔር ህግ ይህ ነው፡ ወይን ከሆነ፡ ተዉት፡ ወይን ያፈራል። ውስጡን በሌላ ነገር ማራባት ትችላላችሁ፡ ብቻ ተዉት እንጂ እንደገና ወደ ቀድሞው ወይን መመለሱ አይቀርም።

190 ስለዚህ ቤተ ክርስቲያንን በጴንጤቆስጣሊዝም፣ በባፕቲስትዝም፣ በሜቶዲስዝም ጋር፣ ከፕሬስባይቴሪያኒዝም ጋር፡ ከ—ከአንግሊካኒዝም፡ እና ከማንኛውም ሌላ ዓይነት ርእዮተ ዓለሞች ጋር አራብተናታል። ለምን አትተዉአትም? ወደ ወይኑ ተመለሱ፣ ወደ ድሮው ሃይል ይመለሳል። አሜን! አሜን! ያንን እወደዋለሁ።

191 "አዲስ ነገር ጀምርን።" እኛም ተመሳሳይ ነገር አደረግን። ሥልጣናችንን ለማሳየት እንሞክር። "ዶክተር **እከሌ-እና-እከሌ** የታላቁ **እከሌ-እና-እከሌ**

ቤተክርስቲያን መሰራች **እከሌ-እና-እከሌ-እና-እከሌ** መሳሰሉት።" ይህ አልነበረም።

192 ሙሴም የተናገረው ያ ነው፡ "ቆይ ምን ማድረግ እንደምችል አሳያቸዋለሁ። ለማንኛውም፡ አደርገዋለሁ!" መታው፡ አላደረገውም። እንደገና ዛተ፡ "ምን ማድረግ እንደምችል አሳያለሁ!" ለዚህም እግዚአብሔር ዋጋውን ሰጠው።

193 አይምሰላችሁ፡ አንተ "ብቻ የሐይማኖት ተቋም ተደገፍ።" እግዚአብሔር ዋጋችሁን ይሰጣችኋል። በትክክል እውነት ነው። ወደ ዋናው መመለስ አለባችሁ። ተመለሱ።

194 (እንዲህ አትበሏቸው፡ "ወደ ቤተ ክርስቲያናችን ኑ። የኛን እምነት ተናገሩ።") ብቻ ለህዝቡ ብቻ ተናገሩ። "ንሰሐ ግቡ ተመለሱ፡ ለኃጢያቶች ስርየት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም ተጠመቅ፥ እና ልባችሁ ቅን ከሆነ፡ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ትቀበላላችሁ። የሚያምኑትም እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል። በአማኞች ወገን ዘንድ፡ እነዚህ ምልክቶች ይሆናሉ።" ለምንድነው? አለቱ፡ የተመታው ዓለት እና የሕይወት ውኃው በትክክል እየፈሰሰ፡ ያኔ ያደረጋቸውን ተመሳሳይ ፍሬዎች እያፈራ ስለሆነ። ሌላ ምንም ማድረግ አይችልም። ኦህ፡ አዎን።

195 እንደው "እኛ ሜቶዲስት፡ እና ባፕቲስቶች ነን፡" እያልን፡ መታየት ያምረናል።

196 ብቻ አለቱን ተናገረው፡ ፍጹም-የማያቋርጥ ነውና። አባል ለመሆን አትሞክር። ከእነዚያ ጋር "አባል" ሆኛለሁ። አባል አትሁን። አንድ እርግጠኛ መሆን ያለብህ ነገር ይህ ነው፡ ይሄኛው ላይ አባል መሆን አይቻልም። የሜቶዲስት አባል መሆን ትችላለህ፡ የባፕቲስት አባል መሆን ትችላለህ፡ ከጴንጤቆስጤዎች ጋር አባል መሆን ትችላለህ፡ ከአንግሊካኖች ጋር አባል መሆን ትችላለህ፣ በዚህ ግን አባል መሆን አይቻልም። አይሆንም። በዚህ መሆን ያለባችሁ መሞላት ነው። በእርሱ ሆናችሁ ተሞሉ እንጂ፡ አባል አትሁኑ። በቃ። በምን ትሞላላችሁ? በኃይል ትሞላላችሁ፡ በመንፈስ ትሞላላችሁ፡ በሕይወት ትሞላላችሁ፡ በደስታ ትሞላላችሁ፡ ሰላም፡ ትዕግሥት፡ ጨዋነት፡ በጎነት፡ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በሕይወታችሁ ትሞላላችሁ፡ የዘላለም መገኛት በዚያ አለና። ልብ በሉ።

እየመሸ ስለሆነ መዝጋት አለብኝ።

197 ይሁን እንጂ፡ ልብ በሉ፡ ያ አለት ፈጽሞ አልተዋቸውም። ፈጽሞ አልተዋቸውም። ክርስቶስም አይተወንም፡ ክርስቶስ እንዲህ አለ፡ "እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ እኔ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ።" ልክ ነው? ያም ዓለት ከኮሬብ ጀምሮ እስከ ኔቦ ድረስ ባለው መንገድ ሁሉ ከእነርሱ ጋር ቆየ። አዎን ቆይቷል። እስከ ዮርዳኖስ ድረስ፡ በዚያ ነበረ። አምላክ ሆይ፡ አቤቱ በዮርዳኖስ ላይ ላየው እፈልጋለሁ!

198 ሙሴ፡ በዮርዳኖስ ሳለ፡ ዓለቱ በመንገዱ ሁሉ ከእርሱ ጋር ነበር። እና እዚያ ቆሞ፡ ወደ ኋላ የተመለሱ እና ከእግዚአብሔር የራቁ ሰዎች ሰ—ሰብስብ እያየ ነበር። ልቡ ይናፍቃቸው ነበር። ዮርዳኖስን ተመለከተ። በዚያም በዮርዳኖስ አጠገብ ነበረ። ዮርዳኖስ, መንፈሳዊ ነገር፡ እያወራሁ ነው። በዚያም ቆሞ ነበር፡ ሞት በእጅጌው እየገባበት ነበር። እርሱ ግን አየና፡ በዚያ በጎኑ የተጋደመው

ዓለቱ በዚያ ነበረ። እርሱም አለቱ ላይ ወጣ፡ መላእክትም መጥተው፡ ገንዘው ወሰዱት።

199 "ከቶ አልጥልህም አልተውህምም።" ዘመኑ የቱንም ያህል ቢከብደን፡ ምንም ያህል ብናረጅም፡ ምንም ዓይነት ሞት ብንሞት እንኳ፡ ዓለቱ በዮርዳኖስ እንደሚሆን፡ ልብ በሉ። በጭራሽ አይተወንም ወይም ፈጽሞ አይለቀንም። ያንን ብቻ ልብ በሉ። ፍጹም-የማያቋርጥ የአለቱ ውኃ በሕይወታችን ሁሉ ከእኛ ጋር ይሆናል፡ እንዲሁም በዮርዳኖስ ይሆናል።

200 ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ። [አንድ ወንድም ምክር ሰጠ—አርታዒ።]

201 ይህ መንፈስ በመካከላችን እየተመላለሰ፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በመካከላችን እየተመላለሰ ባለበት በዚህ ጊዜ፡ ዛሬ ጠዋት ክርስቶስን የማያውቁ እዚህ ይኖሩ ይሆን፡ እንዲሁም እ—እናንተ ወደ አለቱ ያልተጠጋችሁ፡ ከእርሱ ጋር በጥሩ ግንኙነት ያልሆኑ ይኖሩ ይሆን? ህያው እንደሆነ ግን እወቁ። በሁሉም ቦታ እንዴት እንደሚሠራ ተመልከቱ፡ በሁሉም ቦታ እንዴት እንደሚንቀሳቀስ ተመልከቱ፡ በሰዎች ላይ እንዴት እንደሚሰራ ተመልከቱ። ያም ፍጹም-የማያቋርጥ ውኃ ነው። ያ መዳን ነው። ጽዋዎቻቸውን ሞልቶ ዝም ማለት እስኪያቅታቸው ድረስ ሞልቶ የሚፈሰው መንፈስ ነው፡ የሆነ ነገር መምጣት አለበት። እሱን የማታውቁት ከሆናችሁ፡ እባካችሁ እጆቻችሁን ከፍ አድርጋችሁ እንዲህ በሉ፡ "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ጸልይልኝ። አሁን እሱን ማወቅ እፈልጋለሁ። ከእርሱ ጋር መነጋገር እፈልጋለሁ፣ እናም በመንፈሱ ሙላት እሱን ማወቅ እፈልጋለሁ። እሱ ሁል ጊዜ፡ ከጎኔ እንደሆነ ማወቅ እፈልጋለሁ፡ ከጎኔ እንደሆነም አምናለሁ። ግን ከእሱ ጋር ጥሩ ግንኙነት መፍጠር እፈልጋለሁ። እግዚአብሔርን ተጠምቻለሁ፡ እና እራበዋለሁ። እሱን የበለጠ ማወቅ እፈልጋለሁ"?

202 ጌታ ይባርክህ፡ ወዳጄ። አንተም ጌታ ይባርክህ፡ ወዳጄ። አንተም፡ ወንድሜ። አንቺም፡ አዎን፣ ከኋላ ጥግ ላይም። እዚህ ታች፣ እመቤት፣ አዎ። አዎን፡ እመቤት። እኛ እጆቻችሁን እናያለን፡ እግዚአብሔርም ያያችኋል። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወጣት። እግዚአብሔር ይባርክህ። አንቺም፡ እመቤት። ኣሜን። እግዚአብሔር ይባርክሽ። እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እህቴ። ሌላ ሰው ካለ፡ በዚህ የዝምታ ጊዜ። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ እዛ ጋር ያለኸው፡ ወጣቱ።

203 አስቡበት። እስቲ አስቡት፡ ፍጹም-የማያቋርጥ ከአለቱ የወጣ ውኃ፡ ተመሳሳይ መንፈስ፥ ፍርዳችንን በተቀበለ ጊዜ፡ ስለ ፍርዱ በዚያ በታላቅ ጩኸት የጮኸ። የእግዚአብሔር የቁጣ በትር መታው፡ ኃጢአታችሁ በተጠመጠመበት በትር፡ በዚያ ተመታ፡ ከእርሱም ደሙና ውሃው ፈሰሰ። እርሱም፡ "አባት ሆይ፡ መንፈሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ" አለ። በጰንጠቆስጤ ቀንም፡ በጉዞው ሁሉ ከእኛ ጋር ለመሆን መጣ። አሁንም በጣም ቅርባችን ነው።

204 "ከቤት ርቄ ተቅበዝባዥ ነበርኩ፡ ጌታ ሆይ፡ ወደ ቤት እየመጣሁ ነው፡" ማለት አትፈልጉም ወይ? ይህን ስንዘምር፡ አሁንም፡ ወደ መሠዊያው መጥታችሁ፡ ነፍሳችሁን ለክርስቶስ፡ አታሰገዙምን? ኣሜን።

> ከእግዚአብሔር ርቄ ተቅበዝብዣለሁ፡ (ከመንገድ ርቄአለሁ።)

አሁን ወደ ቤት እመጣለሁ፥
እያኹሁ (የአለማመን፡ መንገድ።) ርቄ ተጉዣለሁ፡
ጌታ ሆይ፣ ወደ ቤት እየመጣሁ ነው።

ወደ ቤት እየመጣሁ ነው፡ ወደ ቤት እየመጣሁ ነው፡
ከእግዲህ ላልንከራተት፥
የፍቅር ክንዶችህ በሰፊው ይከፈቱ፡
አሁን፡ ጌታ ሆይ፡ ወደ ቤት እየመጣሁ ነው።

205 [ወንድም ብራንሃም **ጌታ ሆይ፣ ወደ ቤት እየመጣሁ ነው** እያለ አንጎራጎረ—አርታዒ።]

206 ሦስት ታዳጊዎች አይኖቻቸው እንባ እያቀረሩ፡ በፍጥነት፡ ወደ ፊት መጡ፡ በመሠዊያው አጠገብ ተንበርክከዋል። እርግጥ ነው፡ ይቅር ተብለዋል። ገና ከመቀመጫቸው ከመነሣታቸው በፊት፡ በወጣትነት አእምሮአቸው ሀሳባቸውን ሲወስኑ ይቅር ተብለዋል። ህዝቡ ዛሬ ጠዋት፡ ከማን ወገን እንደሆኑ እንዲያውቅላቸው ብቻ፡ ተነስተው ወደዚህ መጥተው፡ ተንበርከኩ።

207 ተመሳሳይ ነገር ለማድረግ የሚፈልጉ አንዳንድ ሽማግሌዎች እንደሚኖሩ አስባለሁ፡ ዝም ብለው ተንበርክከው፡ እንዲህ ይበሉ፡ “ጌታ ሆይ፡ እ—እኔ ከመንገድህ ጠፍቻለሁ። በጣም ብዙ ጥርጣሬዎች ነበሩብኝ፣ እና አንዳንድ ጊዜ ርቄ ተቅበዝብዤ በኃጢአት እወድቅ ነበር። አሁን ጊ—ጊዜ ሳለ መመለስ እፈልጋለሁ። አምላክ ሆይ፣ እኔ—መምጣት እፈልጋለሁ። መጥቼም በእውነት በደስታ እንበረከካለሁ።” ኣሜን።

208 አሁን፡ የአርተር ቢም ሦስት ትናንሽ ልጃገረዶች፡ ተመሳሳይ መጠን ያላቸው፡ ወደዚህ መጥተው፡ ተንበርክከዋል።

209 አንዲት ሴት እየመጣች ነው እሷም እቤት ውስጥ ወንድ ልጅ አላት። በቀደም ቁጭ ብዬ ሳለሁ፡ ሚስተር ውድ መጥቶ ነግሮኛል፡ ይህች እህት ልጅ ለመውለድ ወደ ሆስፒታል እየሄደች እንደሆነ ነገረኝ። መንፈስ ቅዱስም፡ “ሂድና ወንድ ልጅ እንደሚሆን ንገራቸው” አለ። ሲወለድም፡ ትንሽ ልጅ ነበር።

210 ዛሬ ጠዋት እነዚህ ህጻናት፡ በእህት አርኖልድ ክፍል ውስጥ ያሉ ህጻናት፡ ሕይወታቸውን የሰጡ ይመስላሉ። በቀኝ በኩል፡ መሠዊያው በሙሉ፡ በትናንሽ ልጆች ተሞልቷል።

211 ስለ ሌሎቹም ሰዎች፡ ስለ አዋቂዎችም፡ በመሠዊያው ላይ፡ ብንዘምር ጥሩ ነበር።

አሁን፣ ጌታ ሆይ፣ ወደ ቤት እየመጣሁ ነው።

ወደ ቤት እየመጣሁ ነው... (... ? ... )

ከእንግዲህ ላልንከራተት፥
የፍቅር ክንዶችህ በሰፊው ይከፈቱ፡
አሁን፣ ጌታ ሆይ፣ ወደ ቤት እየመጣሁ ነው።

212 ለአፍታ ያህል፡ ለጸሎት፡ ለእነዚህ ህጻናት አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

213 የሰማይ አባት ሆይ፡ ነገ ካለ፡ ኢየሱስ ሌላ አስር ወይም አስራ አምስት አመት ከዘገየ፡ ይህን መልእክት ለሌሎች ትውልዶች የሚያደርሱት እነዚህ

ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ናቸው። ጌታ ሆይ፡ በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ ወደዚህ መሠዊያ መምጣታቸውን እንደሚያስታውሱት፡ በአእምሮዬ ምንም ጥርጥር የለኝም። ጌታ ሆይ፡ እነዚህ ትንንሽ እንቁዎች ናቸው። ዛሬ ጠዋት ታዳጊ ልቦቻቸው እና ለስላሳ ልቦቻቸው ወቀሳቸው። ሙሉውን መልእክት እንኳን አልሰሙም፥ እህታችን አርኖልድ የምትናገረውን እያዳመጧት የነበረውን፡ ክፍል ለቀው ወጡ፥ ሕይወታቸውን ለአንተ ይሰጡ ዘንድ፡ ወደ መሠዊያው መጡ።

214 አሁንም፡ አባት ሆይ፡ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ እንዲኖር መስበኬን ጨርሻለሁ። እናም ይህ መንፈስ ቅዱስ፡ ከዚህ መንፈስ ጋር የተጣመረ እምነት፡ ሁሉንም ነገር ይፈጽማል። አሁንም በዚህች ቅጽበት፡ የሰሩትን ኃጢአት ሁሉ ይቅር እንደምትል እምናለሁ። እና በልቤ ባለው እምነት በሙሉ፣ እለምንሃለሁ፡ በመንገድ ላይ ትንንሿ ህይወታቸውን እንድትከታተል እለምንሃለሁ። ከመንገድ ፈቀቅ አይበሉ።

215 በእውነት ይህ እንግዳ ነገር ነው። መንፈሱ ዛሬ ጥዋት፡ “አንድ እንግዳ ነገር እናያለን” ብሏል። አምላክ ሆይ፣ ከሌሎች ጋር ስራህን ካቆምክ፡ ሕፃናትን ተቀበል። በዚህ ቀን ጠዋት፣ በመሠዊያው ጥሪ ወቅት፣ አንድም ጎልማሳ፣ አንድም ሰው አልመጣም። ይልቁንም፡ ለአዋቂዎችም እንኳን፡ ለመረዳት የሚከብድ መልእክት ነበር፡ ነገር ግን ልጆቹ መንፈሱን አገኙት። ስለ እነርሱ እናመሰግንሃለን፡ አባቴ። እኔ እንደ ባሪያህ፡ ለአንተ ሰጥቻቸዋለሁ፡ የዚህ ስብሰባ ውቴቶች ናቸው፥ ምክንያቱም፣ በሕይወት እስካሉ ድረስ ፈጽሞ-የማያቋርጥ የሕይወት ውኃ በዙሪያቸው እንደሚፈስ አስባለሁ። እግዚአብሔር ከወንበራቸው አንሥቶ ወደዚህ እንደላካቸው፡ አሁን እየሆነ ባለው ነገር ላይ እምነት ይኑራቸው፡ በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ በዚህ አምላክ ላይ እምነት ይኑራቸው። በሞታቸው ቀን መንፈሳቸው ወደ አንተ ይምራቸው፥ በትንሣኤም ቀን ወደ ሥጋቸው ይመለሱ። እነሱ ያንተ ናቸውና፡ አባት ሆይ። በኢየሱስ ስም ለአንተ እናሰረክባቸዋለን።

216 አንገታችንን ደፍተን ሳለ። በመሠዊያው ላይ ያሉትን ትንንሽ ልጆች እጠይቃለሁ፡ በጉባኤው መካከል፡ ኢየሱስ አዳኛችሁ እንደሆነ እና ይህን ሁሉ እንደነገራችሁ የምታምኑ፡ ወደዚህ ለመምጣት በዚህ መሠዊያ ዙሪያ ለመንበርከክ ያመናችሁ። ኢየሱስ እንደሚወዳችሁ እና ሐጢአታችሁን ይቅር እንዳላችሁ ታምናላችሁን? ሁላችሁም ተነስታችሁ ዞራችሁ ታዳሚውን እንድትመለከቱ እፈልጋለሁ። ይህ ማለት፡ ኢየሱስ እንዳዳናችሁ እናንተም እንዳመናችሁት ለሰዎች የምትነግሩበት መንገድ ይህ ነው። አሁን ተነሱ እና በእግሮቻችሁ ቁሙ፡ እና፡ ወደ ጉባኤው ዞራችሁ ተመልከቱ። ኢየሱስን የምትወዱ እናንተ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ሁላችሁ ተነሡ፡ እያንዳንዳችሁ፡ ወደ ጉባኤው ተመልከቱ።

217 እዚህ ፊት ያላችሁ እናንተ ትናንሽ ልጃገረዶችስ? ታምናላችሁን? ኢየሱስን ትወዳላችሁን? እነዚህ ትናንሽ ልጃገረዶች፡ ኢየሱስን በሙሉ ልባችሁ ትወዱታላችሁን? ነው? ትወዱታላችሁ? ትወጂዋለሽ፡ የኔ ማር? ኢየሱስን እንደምትወዱት፡ ሰዎች እንዲያውቁ እዚህ ቁሙ። እግዚአብሄር ይባርካችሁ።

218 አሁን ፊታችን **ወደዚህ** አዙረን ከመሄዳችን በፊት ለእነዚህ ሰዎች እንዘምር፡ “ኢየሱስ እንደ ወደደኝ! መጽሀፍ ቅዱስ፡ ነገረኝ።” አያችሁ? አሁን

እየዘመርን እጆችንን እናንሳ። እሺ፡ እንዘምር።

ኢየሱስ እንደወደደኝ! ይሄን አውቃለሁ፡
መጽሀፍ ቅዱስ ነገረኝ፥
ታናናሾች የርሱ ናቸው።
ደካሞች...

219 አሁን እጆቻችሁን ወደ ላይ አንሱ... ? ... ሁላችንም አንድ ላይ፦

አዎ፡ ኢየሱስ ይወደኛል፡
አዎ፡ ኢየሱስ ይወደኛል፡
አዎ፡ ኢየሱስ ይወደኛል፡
መጽሐፍ ቅዱስ ነግሮኛል።

220 አሁን ሁላችሁም ከኔ በኋላ ትደግማላችሁ፦ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ። ዛሬ፡ እርሱን እንደ ግል አዳኜ ተቀብያለሁ። ከዚህ ቀን ጀምሮ፡ ከአሁን በኋላ፡ እወደዋለሁ እና አገለግለዋለሁ። ኣሜን።

221 [ወንድም ቤን ብራያንት እንዲህ አለ፡ "ወንድም ብራንሃም፣ በዚህ ጊዜ አራት ልጆች በልቤ ውስጥ አሉ። እባክህ ትጸልይላቸው ይሆን? "—እርታዒ።] በእርግጠኝነት፡ ወንድም ቤን።

222 የሰማይ አባት ሆይ፡ ይህ ሰው እነዚህን ሌሎች ህጻናት ወደ ክርስቶስ ሲመጡ አይቷል፡ እና እንደ አባት፡ ሰለ ልጆቹ፡ ድምጹን ያሰማል። እናም እነዚህን ህጻናት ወደ መሠዊያው ያመጣው ይህ መንፈስ፡ ጌታ ሆይ፡ ልጆቹን ያድንላቸው። አድርግለት። አባት ሆይ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ አደራ ለአንተ ሰጠናቸው።

223 አሁን እናንተ ልጆች ወደ መቀመጫችሁ ስትመለሱ፡ በዚያ ረድፍ ላይ ያሉት ሰዎች ሁሉ እነዚህ ትንንሽ ልጆችን እንዲጨብጡ፡ ወይም ሲመለሱ እንዲዳብሷቸው እፈልጋለሁ። ሁላችሁም፡ **በዚህ** መንገድ ወደ ቦታችሁ ተመለሱ። ልጆቹ በሚያልፉ ጊዜ ሁሉም ሰው ትከሻው ላይ ዳብሷቸው። በሙሉ ልባችን እንወዳችኋለን። እናንተ የክርስቶስ አካል ብልቶች ናችሁ፡ እናንተም እንደሌሎቻችን የእሱ አካል ናችሁ።

ወደ ጽዮን ጉዞ ላይ ነን፡
ግርማዊት፡ ግርማዊት ጽዮን፥
ወደ ጽዮን እንወጣለን፡
ግርማዊት የእግዚአብሄር ከተማ።

ኑ፡ ጌታን የምንወድ ሁሉ፡
ደስታችንን እናውጅ፡
በአንድ ልብ አብረን እንዘምር፡
በአንድ ልብ እንዘምር፡
ዙፋኑንም እንከበብ፡
እናም እንከበበው...

በእውነት በጣም የሚያምር መዝሙር ነው! አሁን እጆችንን እናንሣ።

ወደ ጽዮን ጉዞ ላይ ነን፡

ግርማዊት፡ ግርማዊት ጽዮን፥
ወደ ጽዮን እንወጣለን፡
ግርማዊት የእግዚአብሄር ከተማ።

እየዘመርን አሁን እርስ በርሳችን እንጨባበጥ።

ወደ ጽዮን ጉዞ ላይ ነን፡
ግርማዊት፡ ግርማዊት ጽዮን፥
ወደ ጽዮን እንወጣለን፡
ግርማዊት የእግዚአብሄር ከተማ።

224 አሁን እንዲሁ አንገታችን ዝቅ እንዳለ፡ ሁላችንም... ተጫወተው ወንድም ቴዲ፡ እ...

225 እነዚህ የጸሎይት ጥያቄዎች ቀርበውልኛል፡ መሀረብ እና ወዘተ። ከውጭ የሚመጡ ሊኖሩ ይችላሉ። ቢሊ በእንግሊዝ ውስጥ ከሚገኝ ትንሽ ህፃን ልጅ የተላከ ትንሽ ጥንድ ጫማ እንዳለ ነግሮኛል፡ **እቺን** ታክላለች። ህጻኑ ልጅ ሙሉ በሙሉ የአካል ጉዳተኛ ነው። ስለዚህ፡ ለሱም እንጸልያለን።

226 እና ከዚያ... [ወንድም ቤን ብራያንት እንዲህ አለ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ስለማቋረጤ ይቅርታ አድርግልኝ፡ ነገር ግን ትናንት ማታ፡ መኪናችንን በቀኝ የፊት መከላከያዬ ላይ፡ ማን እንደገጨው፡ ይህ እንዲገለጥ ጸልይ። ጌታ እንዲገልጠው ጸልይ።"—እርታዒ።] አሜን፡ ወንድም ቤን፡ እንዲሁ አደርጋለሁ። [ወንድም ብራንሃም **ወደ ጽዮን ጉዞ ላይ ነን** አንጎራጎረ።]

227 ጌታ ሆይ፡ በጉዞአችን ላይ ሳለን፡ የተመታው አለት በአጠገባችን እንዳለ እናውቃለን፡ ፍጹም-የማያቋርጥ ከአለቱ የወጣ ውኃ ከቤተክርስቲያን ጋር እንደሚሄድ እናውቃለን። የዘላለም አምላክ ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት፡ ከእኛ ጋር ባለው በዚህ አምላክ ላይ፡ እምነትን በእኛ ላይ ልቀቅ። በአንተ ዘንድ ሞገስን እንደምናገኝ ሁሉ፡ አንተ በእርሱ ታምነን ዘንድ፡ እንደምትችል አውቃለሁ። አትረፍርፈህ ከሰጠኸን፡ ጌታ ሆይ፡ አላግባብ ልንጠቀምበት እንችላለን። በአንተ ዘንድ ጸጋ ካገኘን ግን፡ ይፈጸም።

228 ወንድማችን እንዳለው አንድ ሰው መኪናውን ገጭቷል። አምላክ ሆይ፡ ለመጠገን የሚያስችል ገንዘብ እንደሌለው እናውቃለን። ይህን ሰው በህሊናው እንድትገሥጸው፡ ወይም ሌላ ነገር፡ ንሰሐ እንዲገባ እና፡ መጥቶ፡ "ወንድሜ፡ መኪናህን አስተካክል፡ የገጨሁብህ እኔ ነኝ፡" ይበለው። ወንድም ቤን እና የሚወዷቸውን ሰዎች እርዳቸው።

229 በዚህም አምላክ አምኜ፡ መሀረብንና ልመናን በእጄ ይዤአለሁ። ሙሴም በእግዚአብሔር አመነ፡ ስለዚህም ባህር ተሻገረ። ዳንኤል በእግዚአብሔር አመነ፡ ከአንበሶች ጉድጓድ ወጣ። ሲድራቅ፡ ሚሳቅና፡ አብደናጎ፡ በእርሱ አመኑ፡ እሳቱም ጠፋ።

230 ጳውሎስ በእሱ አመነ፡ እና አንድ ቀን አገልግሎቶቹ በጣም እጅግ ሲበዛበት ጳውሎስ ወደ ሁሉም ሰው መድረስ ሲሳነው፡ መሀረቦች እየወሰደ፡ "እግዚአብሔር ከእኔ ጋር እንደሆነ አምናለሁ፡" ይል ነበር። ጨርቆች ላይ እና መሀረቦች ላይ እጆቹን ይጭን ነበር፡ የክፉ መናፍስትም ከሰዎች ይርቁ ነበር፥

ደዌና ህመምም ይለቃቸው ነበር። አምላክ ሆይ፡ እኔም በዚሁ አምላክ እምነት አለኝ። ክፉ ይልቀቅ። ጌታ ሆይ፡ ህመም፣ በሽታ፣ እና ደዌ ሁሉ፡ ይልቀቃቸው።

231 በዚያ በወንዙ አጠገብ፡ በእሳት ዓምድ የተናገርከኝ አምላክ አንተ ነህና። ፎቶህን ከእኔ ጋር፡ እዚህ ግድግዳ ላይ እንዲሰቀል ያደረግከው አንተ ነህና። ጌታ ሆይ፡ አንተ ከኛ ጋር ነህ። አንተ ፈጽሞ-የማይቋረጥ፡ ያንን የእሳት አምድ ነህና። እኛም በመንፈስ አንድ ስንሆን፡ ከዚያ አለት የሚፈልቀውን ውኃ ዘወትር እንባረክበታለን። አሁንም፡ እዚህ ህያው ነህ። ጌታ ሆይ፡ በአንተ ዘንድ ድፍረት አለን። እንደምትቀባንና እንደምትረዳን እናምናለን፡ በአንተ ዘንድ እምነት አለን። ለክብራችን አይደለም፡ ጌታ ሆይ፥ ካልሆነ እርሱ መጥፎ ነገር እንዳደረገ፡ እንደ ሙሴ እንሆናለንና። አንተን ለማገዝ፡ አንድ ነገር ማድረግ እንፈልጋለን ጌታ ሆይ። የልባችን ሃሳብ ያ ነው፡ ከቻልን፡ አንተን ለማገዝ ነው። አባት ሆይ፡ እንድናደርግ የምትፈልገውን ሁሉ፡ አሳየን።

232 አሁንም፡ በእምነት ድርጊት፡ እነዚህ መሀረብ የሚወክሉትን ህመም፡ እና እነዚህን ጥያቄዎች እገስጻለሁ። ህዝቡን ጥለው ይሄዳሉ። ጌታ ሆይ፡ እንደምታደርገው አውቃለሁ። እንደምታደርገው፡ በልቤ፡ አምናለሁ። ዛሬ ጠዋት በመካከላችን ያሉትን በሽታዎች ሁሉ ፈውስ።

233 ወደ ዓለቱ፡ ለውሃ፡ መምጣት እፈልጋለሁ ያሉትን እጃቸውን ያነሱትን አድን። አምላኬ ሆይ፡ ዛሬ በጣም ይጠሙ፡ ክርስቶስን እስኪጠሙ ድረስ፡ እንዲህ ያለ የጨው ሕይወት በዙሪያቸው ይኑር። ይሁንላቸው።

234 አባት ሆይ፡ ዛሬ ማታ ከእኛ ጋር ሁን። አምላክ ሆይ፡ በጥያቄዎቻቸው ውስጥ፡ በሰዎች ዘንድ ያለውን፡ እንዳውቅ ስጠኝ። በልባቸው ምንም ነገር ከሌለ፡ ጌታ ሆይ፡ እንግዲያውስ፡ ዛሬ ማታ ልባቸውን የሚነካ የምሰብከውን ነገር ትሰጠኛለህ።

235 ወንድማችንን ኔቪልን፡ ሚስቱን፡ እና ቤተሰቡን፡ ትንሹን ቤተክርስቲያናችንን፡ ባለአደራዎቻችንን፡ ዲያቆናትን፡ ጉባኤያችንን ባርካቸው። እና ደግሞ በሁሉም ቦታ የሚገኘው አካልህ፡ ከኛ ጋር፡ ይሁን አባቴ። ይህንን ለእጆችህ አደራ ስጠን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም።

… ጽዮን፥
ወደ ጽዮን እንወጣለን፡
ግርማዊት የእግዚአብሔር ከተማ።

አሁን በእውነት፡ እንዘምርለት፡ በእውነት አሁን ለእርሱ ይሁን። አያችሁ?

ኑ፡ ጌታን የምንወዱ ሁሉ፡
ደስታችንን እናውጅ፡
በአንድ ልብ አብረን እንዘምር፡
በአንድ ልብ እንዘምር፡
ዙፋኑንም እንከበብ፡
ዙፋኑንም እንከበብ፡

አሁን በተሰበረ ልባችን።

ወደ ጽዮን ጉዞ ላይ ነን።
ግርማዊት፡ ግርማዊት ጽዮን፥

ወደ ጽዮን እንወጣለን፡
ግርማዊት የእግዚአብሔር ከተማ።

61-0723M ፍጹም-የማያቋርጥ ከአለቱ የወጣ ውኃ
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org